ጮራ

መንፈሳዊ መጽሔት

በዓመት አራት ጊዜ የሚታተም ትምህርታዊ ሥነ ጽሑፍ

አሳታሚ:- ማኅበረ በኵር

የመ.ሣ.ቊ. 23956 ኮድ 1000

የስ.ቊ. 011-645-93-59 011-645-63-81 011-646-22-49

011-550-04-50

አዲስ አበባ

የባንክ ሒሳብ:-

የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ልደታ ቅርንጫፍ ቊጥር 1011

ዋና አዘጋጅ ጸጋዬ ደምሴ

ም/ዋና አዘጋጅ ሠርጹ ዕዝለ ጽዮን

ይህ መጽሔት ለማኅበረ በኵር መሥራችና አሰባሳቢ፥ ለጮራ መጽሔትም የመጀመሪያ ዋና አዘጋጅ ለነበሩት ለአለቃ መሠረት ስብሐት ለአብ መታሰቢያ እንዲሆን ተወስኗል::

## ከአሳሳቾች ተጠንቀቁ!

በጮራ መጽሔት ስም ገንዘብ የሚለምኑና የሚቀበሉ ግለሰቦችና ቡድኖች መኖራቸው ይወራልና፥ ከአታላዮች እንድትጠነቀቁ እናሳስባለን:: የእኛ አባሎች የማኅበራችን መታወቂያ አላቸው::

### ለኦርቶዶክሳውያን መልካም ዜና!

ትምህርተ ክርስትና፥
በመላላክ በነጻ ይሰጣል እንደ ገና::

**ለመማር ይፈልጋሉን?**

ሙሉ ስምዎን፥ የመ.ሣ.ቊጥርዎን፥ ገልጸው ይጻፉልን::

የእኛ አድራሻ የመ.ሣ.ቊ. 56307 አዲስ አበባ ነው::

## ማውጫ

| ርእስ | ገጽ |
|---|---|
| ርእሰ አንቀጽ | 1 |
| መሠረተ እምነት | 3 |
| አለቃ ነቅዐ ጥበብና አገልግሎታቸው | 13 |
| ክርስቲያናዊ ምግባር | 20 |
| ናይ ድሕንነት አስተምህሮ | 27 |

## ማስታወቂያ

መጽሔቱን ከአዲስ አበባ ማግኘት የማትችሉና በአድራሻችሁ እንዲላክላችሁ የምትፈልጉ ኹሉ የመጽሔቱን ዋጋና በሬኮማንዴ የሚላክበትን የፖስታ ወጪ በማከል ሙሉ አድራሻችሁን ከሚገልጽ ደብዳቤ ጋር ብትልኩልን እንደታዘዝነው እንፈጽማለን::

የሚቻል ከኾነ በአብያተ ክርስቲያናት በኩል ጥያቄው በደብዳቤ ቢደርሰን የተሻለ ይኾናል::

መጽሔቱን በማሠራጨት ጌታን ማገልገል ለምትፈልጉ ኹሉ እያንዳንዱ እትም (ቊጥር) 50 መጽሔት የሚይዝ እሽግ ኾኖ ስለ ተዘጋጀ እያንዳንዱን እሽግ ለሚገዛ 20% (ከመቶ ሃያ) ቅናሽ ስለሚደረግ ለአሳታሚው ድርጅት የሚከፈለውን 80% (ከመቶ ሰማኒያውን) ብቻ፥ በፖስታ ቤት በኩል የሐዋላውን ከፍላችሁ፤ በቅድሚያ ብትልኩልን ወይም ለባንክ ሒሳባችን ገቢ ብታደርጉልን የምትፈልጉትን ያህል የምንልክላችሁ መኾኑን በትሕትና እንገልጻለን::

የጮራ መጽሔት ማኅበረተኛ መኾን የምትፈልጉ በመ.ሣ.ቊ. 23956 ኮድ 1000 የሦስት መጽሔት ዋጋ እስከ መላኪያው ብር 16.00 ብትልኩ በአድራሻችሁ እንልካለን:: ይህ ማስታወቂያ ለአገር ውስጥ ማኅበረተኞች ብቻ ነው::

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ፥ አሜን

## ርእሰ አንቀጽ

### «ኢይሁብ ክብርየ ለባዕድ፤ - ክብሬን ለሌላ ... አልሰጥም»

ክብር ቀምተው የሚወስዱት፥ ተመኝተው የሚያገኙት ነገር አይደለም። የልዕልና፥ የታላቅነትና የገናናነት መገለጫ ነው። እነዚህ ማንነቶች የሌሉት፥ እነርሱን ተከትሎ የሚመጣ ክብር ባለቤት ሊኾን አይችልም። እግዚአብሔር በቃላት ሊገለጽ እንደማይቻል እንደ ታላቅነቱ መጠን ክብሩም እንዲሁ ገናና ነው። አምልኮ፥ ስግደት፥ ውዳሴ፥ ምስጋና ... ስለ ክብሩ የሚቀርቡ የእርሱ ገንዘቦች ናቸው። እንደርሱ ያለ ማንነት ያለው ከፍጥረት ወገን ከቶ አይገኝምና፥ ለታላቅነቱ የሚሰጠውን ይህን ክብር ሊጋራ የተገባው ወይም የሚችል ፈጽሞ የለም።

ከጥንት ጀምሮ የእግዚአብሔርን ክብር ለራሳቸው ለመውሰድ፥ ሰይጣንና ከአዳምና ከሔዋን ጀምሮ እርሱ ሐሳባቸውን በማሳወር ያንቀሳቀሳቸው ሰዎች ያደረጉት ሙከራ አልተሳካም። አለመሳካት ብቻም ሳይኾን፥ «የቆጡን አወርድ ብላ የብብቷን ጣለች» እንደሚባለው፥ ያልተሰጣቸውንና ያልተገባቸውን ክብር ሲሹ፥ የነበራቸውን ክብር ዐጥተው ተዋርደዋል፤ ኢሳ. 14፥ 12-20፤ ሕዝ. 28፥11-19፤ ዘፍ. 3፥1-19።

እግዚአብሔር ዛሬም አልተለወጠም። በሕያው ቃሉ እንደ ተናገረው፥ ክብሩንና ምስጋናውን ለእርሱ ፍጥረታትም ኾነ፥ አእምሮ የጐደላቸው ሰዎች በልዩ ልዩ መንገድ ፈጥረው ለሚያመልኳቸው ጣዖታት እንዲሰጥበት አይሻም፤ ኢሳ. 42፥8። የእግዚአብሔር ብቻ የኾነውን ክብር፥ ለገዛ ራሴ እወስዳለሁ፡ ወይም ለሌሎች አሳልፌ እሰጣለሁ የሚል ማንም ቢኖር ግን፥ ለክብሩ ቀናተኛ በኾነው አምላክ ቅንአት ይበላል።

አምልኮተ ጣዖት፥ ተሰፍዎተ መናፍስትና የመሳሰሉት አሕዛባዊ ልማዶች፥ መንፈሳዊ ካባ ደርበው በብዙዎቹ ጥንታውያን አብያተ ክርስቲያን መታየት ከጀመሩ ዘመናት ተቈጥረዋል። አምልኮን ለሌላ ሳያጋሩ፥ ለእግዚአብሔር ብቻ እንዲሰጥ ማድረግ የቤተ ክርስቲያን ዋና ተግባር መኾኑ ቢታመንም፥ ችግሩ እየባሰና እየተወሳሰበ ከሚሄድ በቀር መሻሻል አይታይበትም። ለእግዚአብሔር ብቻ የተገባውን ክብርና አምልኮ፡ ጌታን አገልግለው በክብር ላለፉ ቅዱሳን መናፍስት ብቻ ሳይኾን፥ ዛሬ በሕይወተ ሥጋ ለሚገኙ የቤተ ክርስቲያን መሪዎችም እየተሰጠ መኾኑ ይህንኑ ያረጋግጣል።

ጌታን አገልግለው በክብር ያንቀላፉ ቅዱሳን፥ በሕይወተ ሥጋ ሳሉ፥ ለጌታ የተገባውን ክብር ሊወስዱ ቀርቶ የራሳቸውንም ክብር ሳይሹ ትሑታን ኾነው ዐልፈዋል። በምድራዊ አገልግሎታቸው ወቅት እንኳ፥ ከጌታ ታላቅ ስም የተነሣ በእጃቸው የተደረገውን ድንቃድንቅ የተመለከቱ አንዳንዶች፥ እነርሱን ከሰውነት ተራ አውጥተው፥ «አማልክት ሰዎችን መስለው ወደኛ ወርደዋል» ወደሚል ማዕርግ ከፍ አድርገዋቸው ነበር። በአሕዛባዊ ልማዳቸው መሠረትም ሊሠዉላቸውና ሊያመልኳቸው ያደረጉትን ዝግጅት ሐዋርያቱ ያስተዉአቸው በጭንቅ ነው። ያን ጊዜውንም፥ «እኛ ደግሞ እንደ እናንተ የምንስማ ሰዎች ነን፥ ከዚህም ከንቱ ነገር ሰማይና ምድርን ባሕርንም በእነርሱም ያለውን ኹሉ ወደ ፈጠረ ወደ ሕያው እግዚአብሔር ዘወር ትሉ ዘንድ ወንጌልን እንሰብካለን።» ሲሉ ማንነታቸውንና ሊመለክ የሚገባውን እውነተኛ አምላክ ገልጠው ነገሯቸው፤ የሐዋ. 14፥8-17።

እነርሱ እንደ እኛ ያሉ ሰዎች እንጂ ከእኛ የተለዩ አማልክት አለመኾናቸውን፥ በቃልም በሥራም አስተምረውን ዐልፈዋል። በምድር ሳሉ የእግዚአብሔርን የክብሩን ጫፍ ከቶ አልነኩም። ካንቀላፉ በኋላም ቢኾን፡ ቀድሞ ያደርጉት ከነበረው በበለጠ ኹኔታ ለጌታ ክብር ዘብ እንደሚቆሙ አይጠረጠርም። ዛሬ

በስማቸው እየተደረገ ያለውን ቢመለከቱ ግን፥ ቅዱሳኑ ምን ያህል ያዝኑ ይኾን? ሚስቱ ራሔል ልጅ ባለመውለዷ ተበሳጭታ፥ ባሏ ያዕቆብን «ልጅ ስጠኝ ይህስ ካልኾነ እሞታለሁ» ባለችው ጊዜ፥ እርሱም ተቈጥቶ፥ «በውኑ እኔ የሆድን ፍሬ በነሣሽ በእግዚአብሔር ቦታ ነኝን?» በማለት የመለሰላት ያዕቆብ፥ አእምሮ የጐደላቸው ሰዎች ዛሬ ወደ እርሱ ስእለት እንደሚሳሉ ቢያውቅ ምን ይሰማው ይኾን? የመንገድ ጠራጊነት ተልእኮውን የፈጸመውና «እናንተ: - 'እኔ ክርስቶስ አይደለሁም ነገር ግን ከእርሱ በፊት ተልኬአለሁ' እንዳልሁ ራሳችሁ ትመሰክሩልኛላችሁ:: ሙሽራይቱ ያለችው እርሱ ሙሽራ ነው፤ ቆሞ የሚሰማው ሚዜው ግን በሙሽራው ድምፅ እጅግ ደስ ይለዋል:: እንግዲህ ይህ ደስታዬ ተፈጸመ:: እርሱ ሊልቅ፥ እኔ ግን ላንስ ያስፈልጋል::» (ዮሐ. 3፥28-30) ሲል ማንነቱን በገሃድ ያሳወቀው መጥምቁ ዮሐንስ፥ ዛሬ በስሙ እየተፈጸመ ያለውን ቢረዳ ምን ይል ይኾን? እንደ እነዚህ ያሉት ሌሎች ቅዱሳን ኹሉ፥ እነርሱ እንኳን ሊቀበሉት ከቶ የማያስቡትንና በስማቸው እየቀረበ ያለውን አምልኮ፥ ምስጋና፥ ስግደት፥ ስእለትና የመሳሰለውን ኹሉ ማየት ቢችሉ ምን ያህል ያዝኑ ይኾን?

ይህ ብቻ አይደለም:: ትናንትም ኾነ ዛሬ፥ 'በሐዋርያት እግር ተተክተናል' የሚሉ የሃይማኖት መሪዎች፥ 'ለእኔ የእግዚአብሔር ክብር ይገባኛል' ብለው አፍ አውጥተው ባይናገሩም፥ በተግባር ግን በጠራራ ፀሓይ የእግዚአብሔርን ክብር ለራሳቸው ሲወስዱ እየተስተዋለ ነው:: በልዩ ልዩ ክብረ በዓላት ላይ ሲገኙ፥ ከእግዚአብሔር መገኘት ይልቅ ለእነርሱ መገኘት ትልቅ ቦታ ይሰጣል:: ከእግዚአብሔር ይልቅ የእነርሱ ስም ጐልቶ ተደጋግሞ ይጠራል:: ከእግዚአብሔር ይልቅ በስግደት የታጀበ ክብርና ውዳሴ የሚዥጐደጐደው ለእነርሱ ነው:: እግዚአብሔርን ዘወትር በዐዲስ ምስጋና ለማመስገን ታስቦ የተዘጋጀው «ቅኔ»ም፥ የእነርሱው መመስገኛና መመለኪያ ከኾነ ዘመናት ተቈጥረዋል:: ታዲያ ይህን «መመለክ» እንጂ ሌላ ምን ይሉታል!

ለመኾኑ በሐዋርያት እግር ተተክተናል የሚሉ የሃይማኖት መሪዎች፥ ስለሚሰጣቸው መጠን የለሽ ክብር ምን ይሰማቸው ይኾን? 'ለሃይማኖት መሪነታችን የሚገባውን ክብር ነው የተቀበልነው እንጂ ሌላ አይደለም' ብለው ራሳቸውን ይከላከሉ ይኾን? በውኑ እነርሱ «ከተኳቸው» ከሐዋርያት መካከል፥ ክብር ለእግዚአብሔር ብቻ እንዲሰጥ ከመጋደል በቀር የእግዚአብሔርን ክብር የወሰደ ማነው? «ክብር ለሚገባው ክብርን ስጡ::» (ሮሜ 13፥7) ይላል ብሎ በመጥቀስስ ይህን ስሕተት ለመሸፈን ይቻላልን?

ለመሾም ለመሸለም ብለው የሌላቸውን ክብር እየሰጡ፥ በፈጣሪ ምስጋና የሚያመሰግኗቸው «አገልጋዮችስ» ምን ይላሉ? የእግዚአብሔርን ነገር እርግፍ አድርገው ትተው፥ ለእነርሱ የሚያቀርቡትን ክብርና ምስጋና፥ ለሹመት ለሽልማት እንዳቀረቡት እጅ መንሻ ይቈጥሩት ይኾን? ወይስ በየመሸታ ቤቱ መሰንቆ እየሰነቃ፥ ግጥም በመደርደር ለሰዎች የሌላቸውን ክብር እየሰጠና እያስደሰታቸው ገንዘብ በሚሸለም አዝማሪ ስፍራ ሳያውቁት ራሳቸውን አስቀምጠው ይኾን? እርግጥ የሃይማኖት መሪዎች እንደ ሐዋርያት የአምላክን ቀርቶ ያላቸውን ክብር እንኳ ጥለው ምሳሌ ለመኾን ባለመቻላቸው፥ 'ክብር እንስጣችሁ' የሚሉትን ኹሉ ባለመገሠጻቸውና ክብርን ለእግዚአብሔር ብቻ መስጠት እንዲገባም ባለማስተማራቸው ይበልጥ ተጠያቂ ናቸው፤ ይኹን እንጂ የማይገባቸውን ክብር የሚሰጠውም ክፍል በእግዚአብሔር ችሎት ከመጠየቅ አያመልጥም::

«እኔ እግዚአብሔር ነኝ፤ ስሜ ይህ ነው፤ ክብሬን ለሌላ፥ ምስጋናዬንም ለተቀረጹ ምስሎች አልሰጥም::»

ኢሳ. 42፥8::

# መሠረተ እምነት

**ከእምነት መግለጫ ወደ ምእላደ ትምህርተ መለኮት**
**ከነቅዐ ጥበብ**

ባለፈው እትም ስለ እግዚአብሔር ወልድ በምናጠናበት ርእስ ወደ ምስጢረ ትሥጉት ደርሰን፥ ከዚያም አንቀጸ ተዋሕዶን ተመልክተን እንደ ነበረ እናስታውሳለን፤ በዛሬው እትምም የዚሁ የምስጢረ ትሥጉት ክፍል የኾነው አንቀጸ ድኅን ቀርቧል።

**አንቀጸ ድኅን**
**1.0 መግቢያ**

ከምእት ዓመታት በፊት፥ በተለያዩ ጊዜያት ሊቃውንት ስለ ምስጢረ ትሥጉት ባደባባዮች በቡድን፥ በቡድን፤ በትምህርት ቤቶችም በጓድ፥ በጓድ እየኾኑ ይከራከሩ ስለ ነበር፥ ከዚህ ርእስ በተለይ አንቀጸ ተዋሕዶ ለደቀ መዛሙርት ይበልጥ ግልጽና ጥርት ያለ አስተምህሮ ኾኖ እንዲዘጋጅ ለማድረግ፥ ክርክሩ የሚመሰገን አስተዋፅኦ አድርጓል። በየክርክሩ መደምደሚያ ላይ ረችነትን በጦር ኀይል ለማሳመን በተደረገው ግጭት፥ የሰው ሕይወት ያለፈበት የታሪክ ጠባሳ የሚያሳዝን መኾኑ ባይካድም፥ በየክርክሩ ማብቂያ መገዳደል ባይከተልና የራስን ሐሳብ በነጻ በመግለጽ፥ የሌላውንም በማዳመጥ ብቻ የተወሰነ ለማድረግ ራስን መቈጣጠር ቢቻል ኖሮ፥ ከመከራከሩ «መልካም ነበር» የሚያሰኝ ታሪክ ተወልዶ ነበር። የተወለደውም ይህ አሁን ያለው የአንቀጸ ተዋሕዶ ትምህርት ስለ ኾነ፥ እርሱ ለደረሰው ጕዳት እንደ ማካካሻ ሳይቈጠር ይቀራል? ብለን እንጠይቅ ዘንድ እስከ ማሰብ ያደርሰናል።

አንቀጸ ተዋሕዶ ላይ ብቻ ያነጣጠረው የተጠየቅ እስጥ አገባ፥ በዚህ ርእስ ለሚዘጋጀው የአስተምህሮ ጥራት አስተዋጽኦ ማድረጉ አይከፋም፤ ዳሩ ግን እርሱ ብቻውን የሊቃውንቱንና የደቀ መዛሙርቶቻቸውን አእምሮና ጊዜ በመያዙ፥ የትሥጉትን መኖር አስፈላጊ ያደረገውን መለኮታዊ ዐላማ፥ የሰውን መዳንን የሚናገረው አንቀጸ ድኅን፥ የአንቀጸ ተዋሕዶን ያህል ሳይዳሰስ፥ ሳይቈፈርና ሳይመረመር ታልፏል።

በክርስትና ጅማሮ በተመሰገኑ አበው ሊቃውንት ከተሰበከውና ከተጻፈው በቀር፥ ባለፉት ምእት ዓመታት የዘመኑን ትውልድ ጥያቄ እንዲመልስ አድርጎ ትምህርተ ድኅንን ለማዳበር አልታሰበበትምና አልተሞከረም። ምእመኑ ስመ ተዋሕዶን ለሃይማኖታዊ ወገንተኝነት የሚጠቀምበትን ያህል እንኳ፥ 'ከመለኮትና ትስብእት ተዋሕዶ እኔ ምን ተጠቅሜያለሁ? እድን ዘንድ ምን ተደርጎልኛል? ታዲያ ድኛለሁን? ከዳንሁስ ለምን እቅበዘበዛለሁ? ሰላምና ሐሤት ለምን የሉኝም?' የሚሉ መጠይቆች በነፍሱ እንዲመላለሱበትና በእግዚአብሔር ቃል መሠረት ምላሻቸውን እንዲሰጥባቸው የሚያነሣሡ ሁኔታዎች አልተፈጠሩም።

ታዲያ ምእመኑ ከእግዚአብሔር የተሰጠውን የደኅንነት ዋስትና ባለማወቁ (ዮሐ. 3፥14-18፤ 6፥37-40፤ 10፥9፤ 20፥30-31)፥ ነፍሱ ስለ መዳን ለምታቀርበው ውስጣዊ ጥያቄ ከጭንቀትዋ የሚገላግል ምላሽ የሚሰጣት ካለማግኘቷም በላይ፥ ጥማትዋን በማርካት ፈንታ፥ ልትጠጣው የማይገባትን፥ ብትጠጣውም የማያረካትን፥ እንዲያውም ጥማቷን የሚያባብስ፥ ይባስ ብሎም ሌላ ደዌን የሚያመጣባትን ተውሳክ የያዘ የትምህርት አተላ ከዚህም ከዚያም መጋት ግዴታ ኾኖባት ኖረቹ።

ዳሩ ግን የመለኮትና የትስብእት ተዋሕዶ ይኖር ዘንድ፥ እግዚአብሔር በፍቅሩ የተገደደበት መለኮታዊ ዐላማ፥ ሰዎች በወገን ተከፋፍለው ለመከራከርና ለመገዳደል ምክንያት እንዲኾናቸው ለማድረግ አልነበረም። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የመጣው ሰውን ለማዳን ነውና፤ ማቴ. 20፥28፤ ማር. 10፥45፤ ሉቃ. 9፥56።

**2.0 ቃል ሥጋ ኾነ፤ ለምን?**

ተአምኖታችንን በምናስታውቅበት ጸሎተ ሃይማኖት (የእምነት መግለጫ) ስለ እግዚአብሔር ወልድ በሚናገረው ክፍል፥ «እኛን ሰዎችን ለማዳን ከሰማያት ወረደ፤ በግብረ መንፈስ ቅዱስም ከቅድስት ድንግል ማርያም ከሥጋዋ ሥጋን፥ ከነፍሷ ነፍስን ነሥቶ በመወሐድ ፍጹም ሰው ኾነ።» ተብሏልና፥ ቃለ እግዚብሔር ወልድ ከልዑል መንበሩ ወርዶ ሰው የኾነው እኛን ለማዳን ነው። (አራት ነጥብ)

**3.0 የምንድነው ከምንድን ነው?**

ቅድስት ድንግል ማርያም ለምትፀንሰውና ለምትወልደው ልጅ የምታወጣለት ስም «ኢየሱስ» ሊኾን እንደሚገባ፥ ከመፅነሷ በፊት በመልአኩ በቅዱስ ገብርኤል ተነግሯት ነበር፤ ሉቃ. 1፥31፤ 2፥21። በኋላም በግብረ መንፈስ ቅዱስ መፅነሷን መልአኩ ለዮሴፍ ሲነግረው፥ «እርሱም ሕዝቡን ከኀጢአታቸው ያድናቸዋልና ስሙንም ኢየሱስ ትለዋለህ» ብሎት ስለ ነበረ (ማቴ. 1፥21)፥ ሥግው ቃል፥ ኢየሱስ የተባለው ከዘለዓለም በመለኮታዊ እቅድ የተነደፈውን ሰውን የማዳን ሥራን ለመከወን እንደ ኾነ ቀድሞም አሁንም በፍጹምነትና በእርግጠኛነት ታወቋል፤ 1ጢሞ. 1፥15-16፤ 2ጢሞ. 1፥9-11።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በተወለደባት ሌሊትም፥ መንጋቸውን እየጠበቁ በሜዳ ላደሩ

እረኞች የእግዚአብሔር መልአክ የተናገረው፥ «ዛሬ በዳዊት ከተማ መድኀን ተወልዶላችኋል» የሚል የምሥራች ነበር፤ ሉቃ. 2፥10-11።

ስለ ኾነም «ኢየሱስ» የሚለው የሥግው ቃል መጠሪያ፥ አዳኝነት የኾነውን መሲሓዊ ግብሩን በትክክል ስለሚገልጽና ትርጒሙ «እግዚብሔር መድኀኒት ነው፤ እግዚአብሔር ያድናል፤» ማለት ስለ ኾነ በግእዝና በዐማርኛ «መድኀን፥ መድኀኒ፥ መድኀኔ ዓለም፥ መድኀኒተ ዓለም» ከምንለው ጋር ፍጹም ተመሳይ ስም ነው።

ሰው ሠራሽ መድኀኒት እንዳይደለም ከስሙ መረዳት ይቻላል፤ «እግዚአብሔር ያድናል፤ እግዚአብሔር መድኀኒት ነው» ማለት ነውና። በነቢያት መጻሕፍት፥ «እኔ እግዚአብሔር አምላክህ መድኀኒትህ ነኝ» ባለው መሠረት እግዚአብሔር አምላክ ከሆነው ከክበበ ሥላሴ አንዱ አካል (ህላዌ)፥ እግዚአብሔር ወልድ ከኀጢአትና ከፍዳው ሊያድነን በሥጋ መገለጡን ያረጋግጥልናል፤ መዝ. 62፥1፤ ኢሳ. 25፥9፤ 33፥22፤ 35፥4፤ 43፥3፤ 45፥15-21፤ 49፥25-26፤ 60፥16፤ 63፥8-9፤ ኤር. 23፥5-6፤ 33፥15-16፤ ሉቃ. 1፥68-75።

## 4.0 ኀጢአት ምንድን ነው?

እግዚብሔር ወልድ ሰው ኾኖ የሚያድነን ከኀጢአት ነው ከተባለ፥ «ኀጢአት ምንድር ነው?» ያሰኛል። እያንዳንዱ ተናጋሪና ጸሓፊ፥ የኀጢአትን ምንነት የሚገልጽበት የተለያየ የቃል መግለጫ አለው። በእግዚብሔር ቃል ውስጥም የኀጢአትን ምንነት የሚገልጹ ጥቅሶች ብዙ ናቸው፤ ጥቂቶቹ ኀጢአትን በሚከተለው መንገድ ገልጸውታል፤ ኀጢአት ማለት: -

1. የእግዚአብሔርን ብቸኛ ሉዓላዊነት አለመቀበል፤ ዘፀ. 20፥3፤ ዘዳ. 6፥4፤ 32፥39-41፤ ኤር. 7፥17-19፤ 17፥12፡13።
2. ታዋቂ የኾነውን እውነት መጠራጠር፥ መደበቅም፤ ዘሌ. 5፥1፤ ሮሜ 14፥13፤ 2ተሰ. 2፡11-12።
3. ሕግን መተላለፍ፥ በሕግና በሥርዐት ላይም ማመፅ፤ ዘፍ. 3፥11፤ ዘኊ. 15፥30-31፤ ዕብ. 10፥26-31።
4. ቀናውን ጠማማ ነው፥ ጠማማውንም ቀና ነው ማለት፤ ኢሳ. 5፥20፤ 1ዮሐ. 3፥4።
5. ዐደራን አለመጠበቅ፥ ኀላፊነትን አለ መወጣት፥ ተግባርንም አለመፈጸም፤ ማቴ. 25፡24-30፤ ሉቃ. 12፥42-47፤ ዕብ. 6፥7-8።
6. ኀጢአትን መደበቅ ወይም አለ መናዘዝ፤ ዘሌ. 5፥1፤ ምሳ. 28፥13፤ 1ዮሐ. 1፥9-10።
7. በሕግ ባይታወጅም ለኀሊና ታዋቂ የኾነውን በጎውን አለማድረግ፥ ክፉ እንደ ሆነ ከሚታወቀው ጋርም መተባበር፤ ምሳ. 24፥11፡12፤ 2ቆሮ. 6፥14-18፤ ኤፌ. 5፥6-13፤ ያዕ. 4፥17።
8. እግዚአብሔር ከራሱ ቀጥሎ በቤተ ሰብ፥ በቤተ ክርስቲያንና በሀገር የዘረጋውን፥ ዓለምን በጥበቡ የሚያስተዳድርበትን፥ ኅብረተ ሰብም የተቀበለውን ሥርዐትና ሥልጣን መቃወም፤ ዘፀ. 20፥12፤ 1ቆሮ. 11፥3፤ ኤፌ. 5፥21-24፤ 6፥1-9 (ስለ ቤተ ሰብ)፤ የሐዋ. 20፥28፤ 1ቆሮ. 12፥27-28፤ ዕብ. 13፥7-17 (ስለ ቤተ ክርስቲያን)፤ ሮሜ. 13፥1-7፤ 1ጴጥ. 2፥13-17 (ስለ መንግሥት)።
9. የዋዛንን ከላይ ለተገለጹት የኀጢአት ሥራዎች ማነሣሣትና የራስ ተባባሪ ማድረግ፤ ሮሜ 1፥28-32።
10. የራስ ያልኾነውን፥ ሊኾንም የማይችለውንና የማይገባውን ክብር፥ ገንዘብ፥ ሥልጣን ወዘተ... የራስ ማድረግ፥ ወይም ለማድረግ መመኘትና ማቀድ፥ (ዘፀ. 20፥15-17፤ ማቴ. 5፥21-30፤ ሉቃ. 12፥15፤ ኤፌ. 5፥5) የመሳሰለው ኹሉ ነው።

## 5.0 ኀጢአት እንዴት ተከሠተ ?

ኀጢአት ማለት የእግዚአብሔርን ብቸኛ ሉዓላዊ ባለሥልጣን መኾን አለመቀበልና እርሱ የደነገገውን ሕግ መተላለፍ፥ በጎ እንደ ኾነ የሚታወቀውን ሥራም አለመሥራትና የመሳሰለው መኾኑ በግልጽ ይታወቃል። ኾኖም እነዚህ የተጠቀሱትና የመሳሰሉት ዘርፈ ብዙ የኾኑ የኀጢአት ዐይነቶች ኹሉ፥ ዛሬ በመላው ዓለም በማንኛውም ሰው የተለመዱና እንደ ምርት የሚመረቱ መኾናቸው ይታያል። ታዲያ ሰው እነዚህን የኀጢአት ዐይነቶች ኹሉ ከየት አመጣቸው? መጽሐፍ ቅዱስ «ወበእንተዝ በከመ በኄጋየ አሐዱ ብእሲ ቦአት ኀጢአት ውስተ ዓለም፤ ወበእንተ ይእቲ ኀጢአት መጽአ ሞት ላዕለ ኵሉ ሰብእ። - ስለዚህም በአንዱ (በአዳም) በደል ምክንያት ኀጢአት በሰው ኹሉ እንደ ገባች፥ በዚችም ኀጢአት ምክንያት ሞት በሰው ኹሉ ላይ መጣ (ደረሰ)» ብሏል፤ ሮሜ 5፥12።

ወላጆቻችን በኾኑት በአዳምና በሔዋን ትእዛዝ አፍራሽ መኾን፥ ኀጢአት ወደ ዓለም የገባበት ታሪክ በኦሪት ዘልደት 3፥1-24 ተጽፎአልና በኹሉም ይታወቃል። ያ ኀጢአት ባለማወቅ የተሠራ ስሕተት አልነበረም፤ እግዚአብሔር እንዳይበሉ ከከለከላቸው ዛፍ ይበሉ ዘንድ ምክር የመጣላቸው፥ ራሱን የእግዚአብሔር ወደረኛ ለማድረግ ሞክሮ ከወደቀው፥ ለኀጢአትም የመጀመሪያ ፈጣሪ ከኾነው፥ ቀድሞ መልአክ ከነበረውና በኋላ ሰይጣን ከተባለው ፍጡር ነበር፤ ኢሳ. 14፥12-15፤ ሕዝ. 28፥12-19። ከተከለከለው ዛፍ ቢበሉ እንደሚሞቱ እግዚአብሔር ለወላጆቻችን ነግሮአቸው የነበረ ሲኾን (ዘፍ. 2፥17)፥ ሰይጣን ደግሞ በበኩሉ 'አትሞቱም፤ ብትበሉ

እንዲያውም እንደ እግዚአብሔር ትኾናላችሁ' ነበር ያላቸው፤ ዘፍ. 3÷1-6::

እንግዲህ ወላጆቻችን ግሩምና ድንቅ አድርጎ የፈጠራቸውን፥ በምድር ላይ ገዥዎች እስከ ማድረግ ድረስ ያከበራቸውንና ፍቅሩን የገለጸላቸውን እግዚአብሔርን መውደድና እውነተኛ ለኾነ ቃሉ መታዘዝን ይምረጡ? ወይስ የእግዚአብሔርን አምላክነት ለመቀማት ያስችላል ለተባለው ሰይጣናዊ ምክር ይታዘዙ? በሰከነ አእምሮ ሊታዘዙለት የሚገባውን ጌታ መምረጥ ነበረባቸው:: ኾነናም ለሰይጣን ቃል መታዘዝን መረጡ፤ ታዘዙለትም:: እንግዲህ በዚህ ኹኔታ በምርጫቸው የጌታ ለውጥ አደረጉ፤ ለሌላ ጌታ ዐደሩ::

- ❖ 'ይህን በበላህ ቀን ትሞታለህ' በሚለው አምላካዊ ቃል መሠረት፥ የሕይወታቸው ምንጭ ከኾነው ከእግዚአብሔር በመለየት መንፈሳዊ ሞትን ወዲያው እንደ ሞቱ ግልጽ ነው፤ ከዚያ በኋላ የኖሩት መንፈሳዊ ምዉት ኾነው ነበርና፤ ዘፍ. 2÷17፤ ኤፌ. 2÷1:2::
- ❖ በኀጢአት ከወደቁ በኋላም «ዐፈር ነህና ወደ ዐፈር ትመለሳለህ» በተባለው መሠረት የነፍስና የሥጋ መለያየት፥ በሥጋ የርደተ መቃብር፥ በነፍስም የርደተ ሲዖል ፍርድ ተላለፈባቸው፤ ዘፍ. 3÷19፤ ሮሜ 5÷12::
- ❖ በመጨረሻም በትንሣኤ ዘጉባኤ በነፍስና በሥጋ ለዘላለም ወደ ገሃነመ እሳት መውረድ ይጠብቃቸዋል፤ ማቴ. 10÷28፤ ዮሐ. 5÷28-29::

## 6.0 ኀጢአትና ፍዳው በአዳምና በሔዋን ዘር ላይ

«ሰው ለተሸነፈለት ለዚያ ነገር ባርያ ነው» 2ጴጥ. 2÷19:: በመታለል ይሸነፍ በትግል ይሸነፍ፥ ዐውቆም ይሸነፍ በማናቸውም መንገድ ተሸንፎ የተማረከ ሰው፥ ላሸነፈውና ለማረከው ጌታው ባርያ መኾኑ ሁል ጊዜ የሚታይ እውነት ነው:: ተሸናፊው ከዚህ በኋላ የሚኖረው፥ ነጻ በነበረበት ጊዜ ይተዳደርበት በነበረው ሕግ ሳይኾን፥ ባርያ ያደረገው ጌታው በሚያወጣለት ሕግ ነው:: ጳውሎስ የኤፌሶን ምእመናን እንደ ሌላው ሰው ኹሉ በኀጢአታቸው ምክንያት ሙታን እንደ ኾኑ ከገለጸላቸው በኋላ፥ «የዓለምን ክፉ መንገድ ተከትላችሁ በአየር ላይ ላሉት መንፈሳውያን ኀይላት ገዢ ለኾነውና አሁንም ለእግዚአብሔር በማይታዘዙት ሰዎች ላይ ለሚሠራው መንፈስ እየታዘዛችሁ ትኖሩ ነበር» ያላቸው ስለዚህ ነው፤ ኤፌ .2÷1-3 (ዐዲሱ መደበኛ ትርጒም (ዐ.መ.ት))::

የሰው ዘር፥ ወላጆቹ አዳምና ሔዋን ወደው ለገቡበት ኀጢአት ባርያ ኾኖ መገኘቱ፥ በልደት እንደ ተወረሰ ጠባይዓዊ ግዴታ መኾኑን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሲያስረዳ፥ «እናንተ ከአባታችሁ ከዲያብሎስ ናችሁ፥ የአባታችሁንም ምኞት ልታደርጉ ትወዳላችሁ፤ እርሱ ከመጀመሪያ ነፍሰ ገዳይ ነበረ፤ እውነትም በእርሱ ስለ ሌለ በእውነት አልቆመም፤ ሐሰትን ሲናገር ከራሱ ይናገራል፥ ሐሰተኛ የሐሰትም አባት ነውና::» ብሏል፤ ዮሐ. 8÷44::

አዳምና ሔዋን ለልጆቻቸው ያወረሷቸው ይህንኑ በኀጢአት የተበከለ ጠባይዕንና ለሰይጣን መገዛትን በውዴታ የተቀበለ የባርነት መንፈስን ሲኾን፥ ይህን ተፈጥሮአዊ ጠባይ የበከለው ኀጢአት፥ ወደ አዳምና ሔዋን የመጣውም ከሰይጣን በመኾኑ፥ አይሁድ የኀጢአትን ዘር በአዳምና በሔዋን ልብ ለዘራው ለዲያብሎስ ልጆች ይባሉ ዘንድ ተገቢ ኾኖ ተገኘ::

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ይህን ኹኔታ በተክል ምሳሌ አስረድቷል:: የአንድ ዛፍ ዝርያ ያንኑ ለእርሱ እንደ ወላጅ አባት ከሚቈጠረው ዛፍ የወረሰውንና የሚጠበቅበትን መራራም ኾነ ጣፋጭ ፍሬ ማፍራት ግዴታው እንደ ኾነ ገልጾታል፥ «ከእሾኽ ወይን፥ ከኵርንችትስ በለስ ይለቀማልን? ... እናንተ የእፉኝት ልጆች ክፉዎች ስትኾኑ መልካም ለመናገር እንዴት ትችላላችሁ?» (ማቴ. 7÷15-19፤ 12÷33-35) ብሎ፥ ከአዳምና ከሔዋን የተወለድን ሰዎችን ኹሉ፥ ራሳችንን በሚያሳይ ምሳሌ ማንነታችንን እንድናውቅ አድርጓል::

ሰዎች ኹሉ ከአንድ ምንጭ የተቀዱ እንደ መኾናቸው፥ ከረከሰው ምንጭ ንጹሕን ውሃ መቅዳት አልተቻለም:: ስለዚህ ኹላችን ከእግዚአብሔር የቅድስና ሚዛን በታች ኾነናል፤ ኢዮ. 14÷4፤ 15÷14-16፤ 25÷4-6:: በተወረሰው ኀጢአተኛ ጠባይዕ ምክንያትም፥ ዕድሜው ካልፈቀደለት በቀር፥ የኀጢአትን ፍሬ ያላፈራ የለም፤ 1ነገ. 8÷46፤ ኢዮ. 4÷17-19፤ መዝ. 14÷2-6፤ ምሳ. 20÷9፤ መክ. 7÷20፤ 1ዮሐ. 1÷8-10::

## 7.0 በሰው ኹሉ ላይ የሞት ሥልጣን ምክንያት

አባቶች «ጥንተ አብሶ» በሚል ስያሜ የሚገልጹትን በኀጢአት የተበላሸ ተፈጥሮአዊ ጠባይዕን ወርሶ ከመወለዱ የተነሣ፥ ሰው ኹሉ በሐሳብ፥ በቃል፥ በሥራ (በኀልዮ፥ በነቢብ፥ በገቢር) ከኀጢአተኛ ጠባይዕ የተነሣ የኀጢአትን ፍሬ ከማፍራት ነጻ ባለመኾኑ፥ ኀጢአትን ተከትሎና ፍዳ ኀጢአት ኾኖ የመጣውን ሞት የመሞት ግዴታን ጨምሮ ወርሷል:: ገና የተወለዱ ሕፃናት በግላቸው የሚጠየቁበትን ኀጢአት ባይሠሩም፥ ሲወለዱ የወረሱት ባሕርየ ተፈጥሮ ሞት የተፈረደበት በመኾኑ ብቻ ይሞታሉ:: ከዚህ የተነሣም የእግዚአብሔር ቃል፥ «መኑ ሰብእ ዘየሐዩ ወኢይሬእያ ለሞት? ወመኑ ሰብእ ዘያድኅና ለነፍሱ እምእደ ሲኦል? - ሞትን ሳያይ ሕያው ኾኖ የሚኖር ማነው? ነፍሱንስ ወደ ሲኦል ከመውረድ መታደግ የሚችል ማነው?» እያለ ፍዳ ኀጢአት ኾነው ከመጡት ሞትና

መቃብር ሰው ኹሉ ማምለጥ እንደማይችል ይነግረናል፤ መዝ. 89፥48::

ቀድሞ ነጻ ፈቃድ የነበራቸው አዳምና ሔዋን በምርጫቸው ለኀጢአት ተሸንፈው፥ ለኀጢአትና ከኀጢአት በስተ ጀርባ ላለ የኀጢአት ጀማሪ ሰይጣን ራሳቸውን ካስገዙበት ጊዜ ጀምሮ፥ ልጆቻቸውም ያን ነጻ ፈቃድ ማስመለስ አልኾነላቸውም:: «ወኮኑ ሰይጣናት ዉኩላነ ወሥሉጣነ በአዳም ወበኵሉ ዘርዑ ውስተ አህጉሎ ከመ ፂዉዋን:: - ወደ ጥፋት ሲመሯቸው ምርኮኞቻቸው አድርገውም ሊቈጣጠሩዋቸው፥ ሰይጣናት በአዳምና በዘሩ ኹሉ ባለ ሥልጣን ኾኑ፤» ተብሎ በመቅድመ ወንጌል ተጽፎአል:: ይህም ሐሳብ ለኤፌሶን በተጻፈው መልእክት (2፥1-3) ካለው ጋር የተስማማ ነው::

## 8.0 ማንም ማንንም ማዳን አልቻለም

የሮሜ ሊቀ ጳጳሳት አቡሊዲስ፥ እንዲህ ብሏል: -

«ከሰውም ወገን ማንም ማን ሞትን ያጠፋ ዘንድ፥ ትንሣኤንም ይገልጣት ዘንድ አይችልም፤ ዳዊት 'በሕያውነት የሚኖር፥ ሞትንም የማያያት ሰው ማነው? ነፍሱን ከሲኦል፥ ሥጋውንም ከመቃብር የሚያድን ማነው?' ብሎ እንደ ተናገረ:: ራሱን ማዳን ያልተቻለው ሰው ሌላውን ማዳን እንደ ምን ይችላል? አንድ ራሱን ሊያድን ያልቻለ ከኾነስ ዓለምን ኹሉ ሊያድን እንደ ምን ይችላል? ኀጢአት በሰው ዐድሮ ይኖራልና ሞትም ይከተለዋልና::

«ከአዳም አንሥቶ እስከ ሙሴ፥ በአዳም በደል አምሳል ያልበደሉ ሌሎችንም ሰዎች ሞት እንደ ገዛቸው (መጽሐፍ) ተናገረ፤ መጀመሪያ የበደለ አዳም ነው፤ አዳምም በበደለ ጊዜ የሚመስሉትን ያን ጊዜ ወለደ:: ከዚያ ጊዜ ጀምሮም 'አዳም መሬት ነህ ወደ መሬት ትመለሳለህ' የሚል አንድ ዐዋጅ በኹሉ ላይ ተነገረ::» (ሃይ. አበው 42፤8፥7-10)::

በእግዚአብሔር ምሳሌ የተፈጠረው አዳም ልጅን መውለድ የጀመረው፥ ከሰይጣን በመጣ ምክር ራሱን የኀጢአት ባሪያ ካደረገ በኋላ በመኾኑ፥ እንደ ጥንተ ተፈጥሮው የእግዚአብሔር መልክና ምሳሌ ያለውን ነጻ ልጅ መውለድ አልቻለም፤ «አዳምም ኹለት መቶ ሠላሳ ዓመት ኖረ፥ ልጅንም በምሳሌው እንደ መልኩ ወለደ፥ ስሙንም ሴት ብሎ ጠራው፤» ዘፍ. 5፥3:: በጥንት የገባር ሥርዐት «የገባር ልጅ ገባር» ይባል እንደ ነበረው ኾነ::

## 9.0 የእግዚአብሔር የማዳን ተስፋ

አምላካችን ልዑል እግዚአብሔር ከመነገርም፥ ከመደነቅም በላይ ከኾነው ታላቅ ፍቅሩ የተነሣ፥ ለሰይጣን ምክር ተሸንፎ ኀጢአትንና ሞትን በምርጫ በራሱ ላይ ያመጣው የሰው ዘር፥ እንደ ጠፋ ይቀር ዘንድ አልወደደም:: ከወደቀበትና ከሰመጠበት፥ በጨለማው ሥልጣን አገዛዝ ሥር ካለው የኀጢአትና የሞት ጥልቀት ውስጥ፥ በራሱ ጥበብና ኀይል ሊወጣ እንደማይችል አስቀድሞ ዐውቋልና፥ ረድኤትን ሊልክለትና ሊያወጣው፥ ፈጽሞም ሊያድነው ወሰነ::

«ወፈቀደ እግዚአብሔር አድኅኖተ ዓለም በሣህሉ ወበምሕረቱ:: ወርእየ ተግባረ እደዊሁ እለ አምጽአሙ እምተኀጥኦ ኀበ ተረክቦ፤ ወአክበሮሙ ላዕለ ኵሉ ፍጥረት ዘታሕተ ሰማይ ከመ በዝኅት ወፈድፈደት ኀበ ተዔውዖተ ሰይጣን ወተቀንዮቱ መሪር:: - በይቅርታውና በቸርነቱ ብዛት እግዚአብሔር ዓለምን ያድን ዘንድ ወደደ:: ካለመኖር ወደ መኖር አምጥቶ የፈጠራቸውና ከሰማይ በታች ባሉ ፍጥረታት ኹሉ ላይ ያሠለጠናቸው (ሥልጣን የሰጣቸው) የእጅ ሥራዎቹ የኾኑት ሰዎች የሰይጣን ምርኮኛ መኾን እንደ ጸናባቸው፥ አገዛዙም እንደ ከበደባቸው አይቶአልና ሊያድናቸው ወደደ::» (መቅድመ ወንጌል)::

## 10.0 የማዳን ውሳኔው ምንጭ ራሱ እግዚአብሔር ነው

መጽሐፍ ቅዱስ፥ «ክርስቶስኒ መጽአ በዕድሜሁ ይሙት በእንተ ኀጢአትነ እንዘ ኃጥኣን ንሕነ:: ... እንዘ ኃጥኣን ንሕነ ክርስቶስ ሞተ በእንቲኣነ:: ... ወሶበ እንዘ ፀሩ ንሕነ ለእግዚአብሔር ተሠሀለነ በሞተ ወልዱ::» «ወዝንቱ ውእቱ ፍቅሩ ለእግዚአብሔር፥ አኮ ንሕነ ዘአፍቀርናሁ፥ አላ ውእቱ አፍቀረነ፤ ወፈነዎ ለወልዱ ይሕድግ ለነ ኀጣውኢነ::» (ሮሜ 5፥6-10፤ 1ዮሐ. 4፥10) ስለሚል፥ ገና ደካሞች ሳለን፥ ገና ኀጢአተኞች ሳለን፥ ገና ጠላቶቹ ሳለን፥ እግዚአብሔር ልጁን ልኮ የኀጢአታችንን ፍዳ እንዲከፍልና እንዲያድነን ለማድረግ የተነሣሣው ከራሱ በራሱ ብቻ ነው::

## 11.0 ፍትሐዊነትና ሕጋዊነት የሰፈነበት ማዳን

ዘማሪው፥ «ምሕረትና እውነት በፊትህ ይሄዳሉ፤ የዙፋንህ መሠረት ፍትሕና ርትዕ ናቸው፤» (መዝ. 89፥14) እንዳለው፥ እግዚአብሔር ምሕረቱንና ይቅር ባይነቱን በሥራ ላይ አውሎ ሰውን ሊያድን የወሰነበት መንገድ ፍጹም ሕጋዊነት የሰፈነበት አሠራር ነው::

በመቅድመ ወንጌልም እንደ ተገለጸው ምድራዊ ባለሥልጣን ቢኾን ኖሮ፥ 'የበደልህና የሸፈትህ ምሕረት ተደርጎልሃልና ግባና ሰላማዊ ሕይወትህን ቀጥል' ብሎ በሚያውጀው የምሕረት ዐዋጅ፥ ወንጀለኞች ወደየሥፍራቸውና ሥራቸው በተመለሱ ነበር:: ፍትሕ ርትዕን የዙፋኑ መሠረት ያደረገው እግዚአብሔር ግን፥ በደልን የሚያጥብ ካሣ እንዲከፈል ሳያደርግ ኀጢአትን አልሠረዘም:: በደሉን ማጠብ የሚችል ካሣም ኀጢአተኛው ሊከፍል እንደማይችል ያውቃልና፥ ካሣውን ራሱ ከፍሎለት በኀጢአቱ ተጠያቂ ከመኾን ሊያድነው ወሰነ:: «ወበድልወት ኮነ ኵነኔ እግዚአብሔር ወአድኀነነ በፍትሐ ጽድቅ ወርትዕ:: - የእግዚአብሔር ፍርድ ፍትሐዊነትን የጠበቀ ኾነ፤ እውነትና ቅንነት ባልተጓደለበት ፍትሕ አዳነን::» ተባለ::

## 12.0 የአሪት መታወጅ አስፈላጊነት

ኀጢአተኛውን የሰው ዘር ለማዳን፥ እግዚአብሔር በኀጢአተኛው ሰው ቦታ ተተክቶ በደሉን የሚያጥብ ካሣ ይከፍልለት ዘንድ ምን ያህል አስፈላጊ እንደ ኾነ፥ ሰው ይረዳ ዘንድ የኦሪት መታወጅ ትልቅ ሚና ነበረው:: ኀሊናው

በኀጢአት ለደነዘዘበት የሰው ዘር ንቃት ለመስጠትና የኀጢአትን አስከፊነት ለማሳየት የኦሪት መታወጅ አስፈላጊ ኾነ፡፡ ኀጢአት ጠባይዓዊ ሕግ በኾነበትና፥ «ኵሉ ዐመፀ፥ በአንድነትም ረከሱ» (መዝ. 14፥3) በተባለበት ዓለም፥ ኀጢአትን እንደ ኀጢአት ያለ መቍጠር ድንዛዜ የሰውን ኅሊና አጨልሞት ነበር፤ ስለ ኾነም: -

## 12.1 በኦሪት የኀጢአት ምንነት ተገለጠ

እግዚአብሔር ሕጉን ሲሰጥ ሰዎች የሚገኙበት ኹኔታ ከራሱ ጋር ኅብረት ለማድረግ እንደማያበቃቸው በአራት ደረጃዎች አስረዳ፡፡

ሀ. «እግዚአብሔርም ሙሴን አለው፥ ወደ ሕዝቡ ሂድ፤ ዛሬና ነገም ቀድሳቸው፥ ልብሳቸውንም ይጠቡ፥ በሦስተኛው ቀን ሕዝቡ ኹሉ ሲያዩ እግዚአብሔር በሲና ተራራ ላይ ይወርዳልና ለሦስተኛው ቀን ይዘጋጁ!» (ዘፀ. 19፥10:11)፡፡ ከእግዚአብሔር ጋር ለመገናኘት መቀደስ እንዳለባቸው አመለከታቸው፡፡ ሊገናኛቸው የወሰነው እግዚአብሔር ቅዱስ ሲኾን፥ ሰዎች ግን ርኩሳን ኾነዋልና ከነርኩሰታቸው መገናኘት ስለማይችሉ መቀደስ ግዴታቸው መኾኑን ነገረው፡፡

ለ. ለመቀደስ ያበቃል ያሉትን ካደረጉ በኋላም ቢኾን፥ እግዚአብሔር የሚገለጽበትን ተራራ እግርጌ መንካት አልተፈቀደላቸውም፡፡ «ወሰንም ለሕዝቡ በዚያው አድርግላቸው፥ ወደ ተራራው እንዳትወጡ፥ ጫፉንም (የእግርጌውንም ጠርዝ) እንዳትነኩ ተጠንቀቁ፥ ተራራውንም የነካ ይሞታል፤» አላቸው፤ ዘፀ. 19፥12:13፡፡ ርኩሰታቸው በእነርሱ ደረጃ ከተደረገው ሥጋዊ ቅድስና በላይ የሚጠይቅ እንደ ኾነ ያጠይቃል፡፡

ሐ. እግዚአብሔር የተገለጸበት ግርማ ኀጢአተኛው ሰው ይቀርበው ዘንድ የሚጋብዝ አልነበረም፤ በዘፀ. 19፥16-18 ታሪኩ ተጽፎአል፡፡

- የጨለመ ደመና ተራራውን ሸፈነው፤
- ነጐድጓድና መብረቅ፥ እጅግም ብርቱ የመለከት ድምፅ ተራራውን አናወጡት፤
- የሲና ተራራ በእሳት ስለ ተቃጠለ የሚትጐለጐል ጢስ ወጣ፤
- ተራራው ራደ፥ ተናወጠ፤
- ጭጋግ፥ ጨለማ፥ ዐውሎ ነፋስም አካባቢውን አናወጠው፤
- መካከለኛው (አገናኙ) ሙሴም እንኳ፥ «እጅግ እፈራለሁ፤ እንቀጠቀጥማለሁ አለ፡፡» መዝ. 68፥7:8፤ ዕብ 12፥ 18-21፡፡

መ. በሕጉ ቃል ውስጥም እግዚአብሔር የሰውን ኀጢአተኝነት እያሳየ ነበረ፤ ዘፀ. 20፥3-17፡፡ ለምሳሌ: -

- «ከእኔ በቀር ሌሎች አማልክት አይኹኑልህ» ሲል ልታመልክ፥ ልትገዛ፥ ልትታዘዝ የሚገባህ እኔን ብቻ ነው ማለቱ ነበረ፤ ሰው ግን በዔድን ገነት ከነበረበት ጊዜ ጀምሮ እግዚአብሔርን ትቶ ሰይጣንንና ተባባሪዎቹን እየሰማና እየታዘዘ፥ እያመለከም ነበረ፡፡
- «አትስረቅ» ሲልም ያልተሰጠህን፥ ያንተም ያልኾነውን አትንካ፥ አትውሰድ ማለት ሲኾን፥ ሰው ግን ገና በዔድን ገነት በነበረበት ጊዜ ካልተፈቀደለትና ካልተሰጠው ዛፍ ሰርቆ በላ፡፡
- «አትግደል» ተብሏል፡፡ ሰው ግን፥ «ይህን በበላህ ቀን ትሞታለህና መልካምንና ክፉን ከሚያስታውቀው ዛፍ አትብላ» ተብሎና ተከልክሎ ሳለ፥ የተከለከለውን በመብላት ራሱን በመግደል ኀጢአት መሥራቱን ጀመረ፡፡
- «አትመኝ» ተባለ፤ ሰው ግን ፍጡር ባሕርዩ የማይፈቅድለትን ፈጣሪ አምላክ መኾንን ተመኘ፡፡
- «በሐሰት አትመስክር» ተብሏል፡፡ ሰው ግን ስለ ሠራው ኀጢአት እውነትን በመናገር ፈንታ የኀጢአተኛነትን ኀላፊነት ላለመውሰድ ቀላመደ፡፡

እንግዲህ ሰው በሕግ መስተዋትነት ራሱን ሲመለከት፥ ወደ እግዚአብሔር ለመቅረብና ኅብረት ለማድረግ ሊደፍር ይቅርና እንዲያውም፥ «እግዚአብሔር አይናገረን» አለና ቃሉን ለመስማት እንኳ ድፍረት ማጣቱን ተናገረ፤ ዘፀ. 20፥18:19፡፡

ስለዚህም ነው ሐዋርያው ጳውሎስ፥ የኦሪት መታወጅ ሰውን ለማጽደቅ ሳይኾን፥ እንዲያውም ኀጢአተኝነቱን ይበልጥ ለመግለጽ መኾኑን በሚገባ ያስረዳው፤ ሮሜ 3፥20፤ 4፥15፤ 7፥7፤ 1ጢሞ. 1፥8-11፡፡

በሌላም ስፍራ ይኸው ሐዋርያ፥ 'የምድር አሕዛብ የሚባረኩበት የአብርሃም ዘር (ዘፍ. 22፥18) ይመጣ ዘንድ እንዳለው የተነገረው የተስፋ ቃል የሚፈጸምበት ቀን እየተጠበቀ እያለ፥ ሰው የማይባረክባት ኦሪት ትታወጅ ዘንድ ለምን አስፈለገ?' የሚለውን ጥያቄ አቅርቦ መልሱን አስከትሏል፡፡ «ለምንት እንከ መጽአት ኦሪት - እንኪያስ ኦሪት ለምን መጣች? ከመ ታብዝኃ ለኀጢአት እስከ አመ ይበጽሕ ዝኩ ዘርዕ ዘሎቱ አሰፈወ፡፡ - ተስፋ የተነገረለት ዘር እስኪመጣ ድረስ ኀጢአትን ታበዛ ዘንድ ይበልጥ አጐልታ ታሳይ ዘንድ ነው፤» (ገላ. 3፥19) ብሏል፡፡

## 12.2 ኦሪት ወደ ክርስቶስ የመምራት አገልግሎት ፈጻሚ

አቅመ አዳም ያልደረሰ ልጅ፥ መውረስ የሚገባውን ሥልጣንና ሀብት ሊወርስ በሚያስችለው ዕድሜ ላይ እስኪደርስ፥ ከሞግዚት ጠንካራ አስተዳደር ሥር ኾኖ በተግሣጽና በቅጣት በትምህርትም ሥነ ሥርዐት ያለው አስተዳደግ እንዲያገኝ ይደረጋል፡፡ እንደዚሁም የሰው ዘር፥ በአብርሃም ዘር አማካይነት ሊወርስ ቃል የተገባለትን በረከት መውረስ ከሚችልበት የጊዜ ቀጠሮ ላይ እስኪደርስ፥ በሞግዚትነት የሰውን ዘር

እያስተማረችና እየቀጣች ታሳድግ ዘንድ ኦሪት ታወጀች:: «ወዘእንበለ ይብጻሕ አሚን (በኢየሱስ ክርስቶስ) ዐቀበተነ ኦሪት ወመርሐተነ ውስተ አሚን ዘይመጽእ:: ኦሪት እንከ መርሐ ኮነተነ ለኀበ ክርስቶስ!» ገላ. 3፥23-26::

## 12.3 ኦሪት ቤዛ ማስፈለጉን ሰበከች

በኦሪት ዘፀአት፥ ቅዱስ ባሕርዩና ፈቃዱ የተገለጸባቸውን፥ የሕግ ዋነኛውን ክፍል የኾኑትን ዐሥርቱ ቃላትን እግዚአብሔር ሲደነግግ፥ በኦሪት ጠቋሚነት ሰው ምን ያህል እንደ ረከሰ፥ ወደ እርሱ እንዳይቀርብ ኀጢአት ግድግዳ ኾኖ እንደ ከለከለው በግልጽ አስረዳ:: ኀጢአትን በሚጸየፈው በጻድቁ በእግዚአብሔር ፍርድም፥ የኀጢአት ብድራት (ፍዳ) ሞት እንደ ኾነ ሰው ዐውቆ ንስሓ እንዲገባ፥ ይቅርታ እንዲጠይቅና ቤዛ ነፍሱን አቅርቦ ከእግዚአብሔር ጋር እንዲታረቅ የዕርቁን መንገድ አመላከተች:: በኦሪት አመልካችነት ኀጢአት መሥራቱን የተረዳ ሰው፥ በኀጢአቱ ከመጸጸቱና ከክፉ መንገዱ ለመመለስ ከመወሰኑ ጋር፥ (ምሳ. 28፥13) በሠራው ኀጢአት ከሚገባው ቅጣት ያመልጥ ዘንድ የተቈጠረበትን ኀጢአት የሚሸከምለትንና የኀጢአት ደመወዝ የኾነውን ሞት (ሮሜ 6፥23) የሚሞትለትን ቤዛ (ተለዋጭ) ማቅረብ ግዴታው እንደ ኾነ ተነገረው::

እስከዚህ የደረሰ ሰው፥ በእግዚአብሔርና በሕዝቡ መካከል ይቆም ዘንድ ለክህነት አገልግሎት ወደ ተመረጠው ካህን፥ ነውር የሌለበትን ቤዛውን የመሥዋዕት እንስሳ ይዞ ይቀርባል፤ ኀጢአቱን የሚሸከምለት ቤዛው እንደ ኾነ ሲያስረዳ፥ እጁን በእንስሳው ላይ ጭኖ ኀጢአቱን ይናዘዛል:: ካህኑም የታረደውን እንስሳ ደም በመርጨት ያስተሰርይለታል፤ ዘፀ. 29፥10፤ ዘሌ. 1፥4፤ 3፥2:8፤ 4፥4:15:29፤ 16፥20-22::

መሥዋዕት በቀረበበት ኀጢአት የተጠያቂነት ዕዳ ይቀራል፤ እግዚአብሔር በቃሉ የሰጠው የስርየት ማረጋገጫ፥ «ካህኑ ስለ እርሱ ያስተሰርያል፥ እርሱም ይቅር ይባላል!» የሚል ነውና፤ ዘሌ.4፥20:26:31:35፤ 5፥6:10:13:16:18፤ 6፥7::

ሕይወት በሕይወት ሳይለወጥ፥ ደምም ሳይፈስስ ስርየት የለምና፥ በዚህ መንገድ ብቻ ስርየት እንደሚገኝ አመልካች ሕገ መሥዋዕት በኦሪት ዘሌዋውያን ተደነገገ፤ 17፥11፤ ዕብ. 9፥22::

## 12.4 በኦሪት ጥላነት የአካሉ መምጣት ተበሠረ

የኀጢአትን ስርየት ለማግኘት መቅረብ ስላለበት የእንስሳ መሥዋዕት ድንጋጌ የተሰጠበት ብሉይ ኪዳን፥ ምሳሌያዊና ምድራዊ አገልግሎት የሚከናወንበት የጥላ አገልግሎት እንደ ነበረ ተገልጸአል፤ «እስመ ጽላሎታ ይእቲ ኦሪት ለእንተ ትመጽእ ሠናይት፥ እስመ ኢኮነት ለሊሃ» «ወባሕቱ አምሳለ ኮነት ለዝ መዋዕል» እየተባለ በዐዲስ ኪዳን ተነግሯል፤ ዕብ. 9፥9፤ 10፥1::

አማናዊና አካላዊ አገልግሎት ቢኾንማ ኖሮ: -

- ❖ ሕያዊት ነፍስ ላለችው ሰው መቅረብ የነበረበት ቤዛ ነፍስ፥ በደማዊት ነፍስ የሚንቀሳቀስ እንስሳ አልነበረም፤ ቢያንስ የሚመጥነው ሕያዊት ነፍስ ያለችው ሰው መኾን ነበረበት::
- ❖ አስታራቂው (መካከለኛው) ካህን ከኀጢአተኛው ሰው መካከል መኾን አልነበረበትም::
    1. በራሱ በኩል የሚጠየቅበት ኀጢአት የሌለበት፥ ስለ ሌላው ኀጢአተኛ ብቻ የሚማልድና የሚያስታርቅ ሊኾን በተገባው::
    2. ኅሩይ ማእከለ እግዚአብሔር ወሰብእ ለመኾንም ዕሩቅ ብእሲ (ሰው ብቻ) መኾን አልነበረበትም፤ የተበደለውን እግዚአብሔርና በደለኛውን ሰው ለማገናኘት አምላክም ሰውም ኾኖ መገኘት በተገባው፤ 1ጢሞ. 2፥5፤ ዕብ. 7፥28::
    3. አማናዊው ካህን ቢኾን ኖሮ መሥዋዕት ማቅረብ የነበረበት፥ የሰማያዊ መቅደስ ምሳሌ ወይም ጥላ በኾነችው ምድራዊት መቅደስ አልነበረም፤ በአማናዊትና ሰማያዊት መቅደስ አማናዊ መሥዋዕት በአማናዊ ካህን መቅረብ ነበረበት፤ ዕብ. 7፥26-28፤ 8፥1-5::

## 13.0 አማናዊው የዐዲስ ኪዳን አገልግሎት ተገለጠ

«ሰው ዓለምን ኹሉ ቢያተርፍ ነፍሱንም ቢያጕድል ምን ይጠቅመዋል? ሰውስ ስለ ነፍሱ ቤዛ ምን ይሰጣል?» ማር. 8፥36:37::

ሰው ለመዳን ከፈለገ ስለ ነፍሱ ቤዛ (ተለዋጭ) የመስጠት ግዴታ ያለበት ሲኾን፥ ቤዛ መስጠት ካልቻለ ግን በኀጢአቱ ለዘለዓለም በገሃነመ እሳት ሊቀጣ ነው:: ስለ ነፍሱ ቤዛ የመስጠት ግዴታ ያለበት ሰው፥ ዓለምን ኹሉ ቢገዛ፥ ስለ ነፍሱ ቤዛ ዓለምን ኹሉ ቢሰጥ እንኳ፥ በቂ አይኾንምና ዓለምን መግዛቱ ምን ይጠቅመዋል?

ከየትም ኾነ ከየት፥ ማንም ኾነ ማን ለሰዎች አማናዊ ቤዛ ሊኾንልን አልቻለም፤ ባለመኖሩም ከሥላሴ አንዱ አካል እግዚአብሔር ወልድ ቤዛ ኾኖ ያድነን ዘንድ ሰው ኾነ::

## 14.0 ኀጢአትን የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ

በኦሪት ድንጋጌ መሠረት፥ እያንዳንዱ እስራኤላዊ በበደለ ቍጥር ቤዛ ነፍሱን አቅርቦ ይሠዋ ነበር፤ በየዓመቱም ስለ ኹሉ የሚኾን መሥዋዕት ይቀርብ ነበር:: (በኦሪት ዘሌዋውያን ከምዕራፍ 1 እስከ 7 እንዲሁም ምዕራፍ 16 ይመልከቱ) ኢሳይያስ ግን እግዚአብሔር የኹላችንን ኀጢአት የሚያሸክመውን

«የእግዚአብሔር በግ» በማመልከት ተንብዮ ነበር፤ (53÷4-12)።

የተቀጠረው ቀን ሲደርስም የመሲሑ ዐዋጅ ነጋሪና መንገድ ጠራጊ ኾኖ የተገለጠው መጥምቁ ዮሐንስ÷ ከልዑል ዙፋኑ ወርዶ ያድነን ዘንድ በሥጋ ወደ ተገለጠው ወደ ጌታችን ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ እያመለከተ «እነሆ! የዓለምን ኀጢአት የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ» አለና÷ ምሳሌው በአሪት መሥዋዕት የታየው÷ በትንቢትም የተጠቈመው÷ ለዓለም ኹሉ አንድ ጊዜ ይሠዋ ዘንድ ያለው÷ ራሱ ጌታችን ኢየሱስ እንደ ኾነ አረጋገጠ፤ ዮሐ. 1÷29።

## 14.1 የካህናት ውሳኔ

እንደ ቤተ ክርስቲያናችን አቈጣጠር÷ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ 33ኛ ዕድሜ ላይ÷ እንደ ተለመደው የፋሲካ በዓል ሊከበር በተቃረበበት ሰሞን÷ የአይሁድ ሸንጎ ተሰብስቦ ነበር። «ዓለሙ ኹሉ እየተከተለው ነውና በናዝሬቱ ኢየሱስ ምን እናድርግ?» ለሚለው አጀንዳ መፍትሔ የሚኾን ሐሳብ ያገኙ ዘንድ የሸንጎው አባላት ተመካከሩ፤ በኋላም ሊቀ ካህናት ቀያፋ ያቀረበውን ሐሳብ እንደ መፍትሔ ተቀበሉት፤ «እናንተ አኮ ምንም አታውቁም÷ ሕዝቡ ኹሉ ከሚጠፋ ስለ ሕዝቡ አንድ ሰው ቢሞት የሚሻል መኾኑን አታስተውሉም!» ብሎ በትንቢት መንፈስ ተናገረ። ይህም ኹኔታ ሊቀ ካህናቱ ለመሥዋዕት የሚቀርበው እንስሳ ይሠዋ ዘንድ÷ ብቁ መኾኑን አረጋግጦ የመቀበል ኀላፊነቱን እንደ ተወጣ አመላካች ነበር፤ ዮሐ. 11÷45-57።

## 14.2 የራሱ የጌታ ውሳኔ

ጌታ ራሱን አሳልፎ በሚሰጥበት ዕለት ዋዜማ÷ የአይሁድ ፋሲካ እየተከበረ ባለበት ምሽት (ጸሎተ ኀሙስ)÷ ለበዓሉ ከቀረበው መሰናዶ አንዱን ኅብስትና ጽዋ አንሥቶ ለደቀ መዛሙርቱ ሲሰጥ: -

- ❖ ስለ ኀጢአት ስርየት በሚደረገው በእርሱ መሥዋዕት መኾን ዐዲስ ኪዳን መግባቱን ዐወጀ፤ ማቴ. 26÷26-29።
- ❖ ሥጋው እንደ ኅብስቱ የሚቈራረስ÷ ደሙም እንደ ተጨመቀ ወይን የሚፈስስ መኾኑን አመለከተ፤ ማር. 14÷22-25፤ ሉቃ. 22÷19:20።

## 14.3 የሕዝቡ ውሳኔ

በየዓመቱ በፋሲካ በዓል ወንጀለኛ በነጻ ይሰናበት ስለ ነበር÷ ይህ ዕድል÷ ተመርምሮ ኀጢአት ላልተገኘበት ለናዝሬቱ ኢየሱስ ሊሰጥ ይችል እንደ ኾነ ሕዝቡ በተጠየቁ ጊዜ÷ በርባን የተባለው ወንጀለኛ እንዲለቀቅ ወሰኑ። ኢየሱስን ግን «ስቀለው÷ አስወግደው» በማለት ጮኹ። ስለ ሕዝብ ኹሉ ይሞታልና በሞቱ ሕዝቡ ተስማማ፤ ማቴ. 27÷22:23፤ ማር. 15÷12-14፤ ሉቃ. 23÷18-23።

## 14.4 የመንግሥት ውሳኔ

የሮማን መንግሥት ወክሎ ይሁዳን ይገዛ የነበረው ጲላጦስ÷ በችሎቱ የቀረበውን ጌታ ኢየሱስን በመረመረው ጊዜ÷ እንከን እንዳላገኘበት አስታውቆ ነበር፤ ዮሐ. 18÷38-40፤ 19÷4:6።

ነገር ግን ከሳሾቹን ስለ ፈራ ገረፈውና ይሙት በቃውን አጽድቆ ይሰቀል ዘንድ ወሰነ፤ ማቴ 27÷26፤ ማር. 15÷15፤ ሉቃ. 23÷23-25፤ ዮሐ. 19÷16።

## 14.5 የእግዚአብሔር ቍርጥ ውሳኔ

ዓለም ሳይፈጠር የተወሰነው መለኮታዊ ውሳኔ÷ አንዱ ስለ ኹሉ ይሞት ዘንድ ስለ ነበረ÷ ጊዜው ሲደርስም እግዚአብሔር የኹላችንን በደል በልጁ ላይ በማኖር በሞቱ ተስማማ፤ ኢሳ. 53÷4-10፤ ዮሐ. 3÷14-18፤ የሐዋ. 2÷22-23።

## 15.0 ጌታችን በኹለንተናው በመቀጣት የሰውን ዕዳ ከፈለ

በኦሪቱ ድንጋጌ ለመሥዋዕት የሚቀርበው እንስሳ ታርዶ ደሙ እንደሚፈስስና እንደሚረጭ÷ ቆዳው እንደሚገፈፍ÷ ሥጋው እንደሚበለት÷ ስቡ በመሠዊያው ላይ÷ ተራፊውም ከሰፈር ውጪ እንደሚቃጠል ይታወቃል፤ በዚሁ ዐይነት አማናዊው መሥዋዕት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በኹለንተናው በመከራ እቶን ተቃጠለ፤ ዘሌ. 4÷5-12:16-21።

1. በሥጋውና በደማዊት ነፍሱ ተሠቃየ÷
   - ❖ ተያዘ÷ ታሠረ፤ ዮሐ. 18÷12።
   - ❖ በጥፊ ተመታ÷ ተጕሰመ፤ ማቴ. 26÷67:68።
   - ❖ ራሱን በሚወጋው በእሾኽ አክሊል ተሠቃየ፤ ማቴ. 27÷29:30።
   - ❖ ተገረፈ፤ ማር. 15÷15።
   - ❖ መስቀሉን ተሸክሞ ከአደባባይ እስከ ቀራንዮ ተጓዘ፤ ዮሐ. 19÷17፤ ሉቃ. 23÷26።
   - ❖ እጆቹንና እግሮቹን ተቸንክሮ በመስቀል ላይ ተሰቀለ፤ ሉቃ. 23÷33።
   - ❖ «ተጠማሁ» ሲል ሆምጣጤ ተሰጠው፤ ዮሐ. 19÷28:29።
   - ❖ ጎኑን በጦር ተወጋ፤ ዮሐ. 19÷34።
2. በሕያዊት ነፍሱም ተሠቃየ

   ኀጢአታችን ተጫነበት÷ ተሰደበ÷ ተተፋበት÷ አላገጡበት፤ ኢሳ. 53፤ መዝ. 22። ሕያዊት ነፍሱም በውስጡ ተጨነቀች ተከዘች፤ (ሃይ አበው ዘጎርጎርዮስ 61÷11)።
3. ሥቃዩን ኹሉ በአእምሮ ተቀበለው

   የመሥዋዕቱ እንስሳ ዐንገቱ ሲቈረጥ ወዲያው ስለሚሞት÷ ቆዳው ሲገፈፍ÷ ሥጋው ሲበለት÷ በእሳት ሲቃጠል አይሰማውም፤ አያመውም። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ግን÷ ነፍሱን የሰጠው መከራው ኹሉ (ጸዋትወ መስቀል) እየተሰማው ከተቀበለ በኋላ

በመጨረሻ ነው፤ ማቴ. 27፥50፤ ማር. 15፥37፤ ሉቃ. 23፥46፤ ዮሐ. 19፥28-30።

## 16.0 የእግዚአብሔር ቅን ፍርድ

«በከመ ውእቱ ኢገብረ ኀጢአተ ወኢተረክበ ሐሰት ውስተ አፉሁ። እንዘ ይጼዕልዎ ኢጸዐለ፤ ወእንዘ የሐምምዎ ኢተቀየመ፥ አላ አግብአ ርእሶ ለዘይኴንን ጽድቀ። ወበእንተ ኀጣውኢነ ውእቱ ተሰቅለ ዲበ ዕፅ በሥጋሁ ከመ ያውፅአነ እምኀጣውኢነ ወበጽድቁ ያሕይወነ። - እርሱም ኀጢአት አላደረገም፤ ተንኰልም በአፉ አልተገኘ በትም። ሲሰድቡት አልተሳደበም፤ መከራንም ሲቀበል አልዛተም፤ ነገር ግን በጽድቅ ለሚፈርደው ራሱን አሳልፎ ሰጠ፤ ለኀጢአት ሞተን ለጽድቅ እንድንኖር እርሱ ራሱ በሥጋው ኀጢአታችንን በዕንጨት ላይ ተሸከመ።» 1ጴጥ.2፥22-24።

በራሱ በኩል የሚጠየቅበት እንከን ያልተገኘበት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፥ እኛ በኀጢአታችን ምክንያት ልንቀበለው የተገባንን ፍዳ በሙሉ ይከፍልልን ዘንድ በሥጋው ርደተ መቃብርን፥ በነፍሱም ርደተ ሲኦልን በፈቃዱ ተቀበለ። ነቢዩ ዳዊት በመሲሑ ቦታ ኾኖ፥ «ነፍሴን በሲዖል አትተዋትም፥ ቅዱስህንም መበስበስን ያይ ዘንድ አትሰጠውም።» ብሎ አስቀድሞ እንደ ተነበየው፥ በኵረ ትንሣኤ ይኾልንም ዘንድ በመለኮታዊው ቅን ፍርድ ከሞት ተነሣ፤ መዝ. 16፡8-11፤ የሐዋ. 2፡25-32።

## 17.0 ጌታችን አለመታዘዝን በመታዘዝ ካሰ

ፍጡር ግቡር የኾነ ኹሉ ለፈጣሪው መታዘዝ፥ መገዛትም ባሕርያዊ ግዴታው መኾኑ ይታወቃል። ቀዳማዊ አዳም ግን ለፈጣሪው መታዘዝና መገዛት ባሕርያዊ ግዴታው ኾኖ ሳለ፥ የመታዘዝ ግዴታውን ባለመፈጸሙ፥ እግዚአብሔርን በደለ፤ ለራሱና ለዘሩም ሞትን አተረፈ፤ ዘፍ. 2፡17፤ 3፥4-6፡19።

ኾኖም በክበበ ሥላሴ የማዘዝ መለኮታዊ ሥልጣንና መብት እንጂ የመታዘዝ ግዴታ የሌለበት እግዚአብሔር ወልድ፥ ቀዳማዊ አዳም ባለመታዘዝ የፈጸመውን በደል በመታዘዝ ይክስ ዘንድ፥ የመታዘዝ ግዴታውን ያልተወጣውን የአዳምን ባሕርይ ገንዘብ አድርጎ ዳግማዊ አዳም ተሰኘ፤ እስከ መስቀል ሞትም ድረስ ለአባቱ ታዘዘና፥ የአዳምን አለመታዘዝ በመታዘዝ ካሰ፤ ማር. 14፡35፡36፤ ፊልጵ. 2፥6-11።

ቀዳማዊ አዳም ቢታዘዝ ኖሮ ሊያገኝና ለእኛ ለልጆቹም ሊያወርሰን ይችል የነበረውንና ባለመታዘዙ ምክንያት ያጣነውን ዘላለማዊ ሕይወት አስገኝቶ ለምንታዘዝለት ተከታዮቹ ዐደለን፤ 1ቆሮ. 15፥21፡22፤ ዕብ. 5፥8-10።

በመጽሐፍም እንዲህ ተብሎ ተጻፈ፥ «በአንዱ ሰው አለመታዘዝ ብዙዎች ኀጢአተኞች እንደ ኾኑ፥ እንዲሁ ደግሞ በአንዱ መታዘዝ ብዙዎች ጻድቃን ይኾናሉ።» ሮሜ 5፥19።

## 18.0 የዕዳ ስረዛን አስገኘልን

እንዳች እንከን የሌለበት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የሞተው ሞት፥ በበደላችን ምክንያት ልንሞትና በሥጋ ርደተ መቃብርን፥ በነፍስም ርደተ ሲዖልን ልንቀበል ለሚገባን ለእኛ የበደላችን ካሳ ኾኖ እንዲቈጠርልንና እንዲመዘገብልን መለኮታዊ ብይን ተሰጠ። ዲያብሎስ ምንም የሞትና የሲዖል አበጋዝ ቢኾን፥ ከሥልጣኑ ክልል ዐልፎ መሞት የማይገባውን፥ ንጹሑንና ቅዱሱን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን፥ የኀጢአት ፍዳ ኾኖ በመጣው ሞት በመግደሉና በማስገደሉ፥ የሞትና የሲዖል አበጋዝነቱን ተነጠቀ፤ ዲያብሎስ በእግዚአብሔር ቅን ፍርድ ተሸነፈ፤ ዕብ. 2፥14፡15፤ ራእ. 1፥17፡18።

## 19.0 ሥልጣን ኹሉ ለጌታችን ለኢየሱስ ክርስቶስ ኾነ

ከሥላሴ አንዱ ነውና፥ በመለኮትነቱ ያለውን የእግዚአብሔርነት ሥልጣን ሳይጠቀምበት ወስኖ፥ ሰውን ለማዳን ሲል በሰው ቦታ ገብቶ እስከ መስቀል ሞት ራሱን ባዶ ያደረገውን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን፥ ሞትንና ሲዖልን ከአበጋዛቸው ዲያብሎስ ጋር፥ በቅን ፍርድ ድል ካደረገ በኋላ፥ በሰማይና በምድር ያለ ሥልጣን ኹሉ ተሰጠው፤ ኹሉም ከእግሮቹ በታች ተደረገ። ለዚህም ነው ከትንሣኤው በኋላ ወደ ደቀ መዛሙርቱ መጥቶ፥ «ተውህበ ሊተ ኵሉ ኵነኔ በሰማያት ወምድር» ያላቸው፤ ማቴ. 28፥18፤ ፊልጵ. 2፥6-11።

## 20.0 ቤተ ክርስቲያን የምታስተጋባው ዐዋጅ

«ክርስቶስ ተንሥአ እሙታን፥ በዐቢይ ኀይል ወሥልጣን፥ አሰሮ ለሰይጣን፥ አግዐዞ ለአዳም፥ እምይእዜሰ ኮነ ፍሥሓ ወሰላም። - ክርስቶስ በታላቅ ኀይልና ሥልጣን ከሙታን ተነሣ፥ ሰይጣንን አሰረው፥ አዳምን ነጻ አወጣው፤ ከእንግዲህ ወዲህስ ሰላምና ደስታ ሰፈነ።» እያለች በሞቱና በትንሣኤው የተገኘውን የምሥራች ትሰብካለች፤ ታውጃለች ታስተጋባለች።

## 21.0 ከሞት የተነሣው ጌታ ትእዛዝ

ጌታችን፥ አምላካችንና መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከሙታን ተለይቶ ከተነሣ በኋላ፥ ቀዳማዊ አዳም አስወስዶ የነበረውን ገዥነትና ግዛት፥ በዳግማዊ አዳምነቱ በቅን ፍርድ (በፍትሕ ርትዕ) ማስመለሱን ሲገልጽ፥ «ሥልጣን ኹሉ በሰማይና በምድር ተሰጠኝ፤» አለ። በመቀጠልም፥ «እንግዲህ ሂዱና አሕዛብን ኹሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው፥ ያዘዝኋችሁንም ኹሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው፤ እነሆም እኔ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ከእናንተ ጋር ነኝ።» ብሎ «ለዘላለም ድኅነት የኾነውን ቅዱስ ወንጌል ከፀሓይ መውጫ እስከ መጥለቂያው ድረስ በእጃቸው ላከው።» ማቴ. 28፥18-20፤ ማር. 16፥8፡15።

በታማኝነታቸው የተመሰከረላቸው ደቀ መዛሙርትም ሳይጨምሩ፥ ሳይቀንሱም፤ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ ላይ የተመሠረተውን ደኅንነት፥ ሰው በወንጌል

ስብከት አማካይነት በእምነት እንዲቀበል ያስመታከት ሰበኩ፤ ማር. 16÷20፤ 1ቆሮ. 15÷1-4::

## 22.0 ወንጌልን አምኖ በመቀበል የተገኘ በረከት

ወንጌል ማለት ቃለ ብሥራት ነውና በእምነት ለሚቀበለው ኹሉ ያስገኘው በረከት ብዙ ነው: -

- ❖ ወንጌል የሚያምኑትን ኹሉ ለማዳን የሚችል የእግዚአብሔር ኀይል ነውና፥ የተሰበከላቸውን ቃለ ወንጌል ሰምተው የሚያምኑ ኹሉ ከኀጢአትና ከፍዳው ነጻ ይኾናሉ፤ የዘላለም ሕይወት ባለመብት መኾንም ይረጋገጥላቸዋል፤ ዮሐ. 3÷14-18፤ ሮሜ 1÷16፤ 1ቆሮ. 15÷22::
- ❖ የእግዚአብሔር ልጆችና የመንግሥቱ ወራሾች ይኾናሉ፤ ዮሐ. 1÷12፤ ገላ. 4÷6:7፤ 1ዮሐ. 3÷1:2::
- ❖ ወደ እግዚአብሔር ልጆች ኅብረት (ቤተ ክርስቲያን) ይጨመራሉ፤ ዮሐ. 10÷16፤ ኤፌ. 2÷18-22::
- ❖ እግዚአብሔር ዋጋ የከፈለባቸው ዕድል ፈንታው መኾናቸውን የሚያረጋግጠውን ማኅተመ መንፈስ ቅዱስ ያትምባቸዋል (መንፈሱን ያሳድርባቸዋል)፤ 1ቆሮ. 6÷19:20፤ 2ቆሮ. 1÷21:22::
- ❖ የእግዚአብሔር ልጆች ኾነዋልና፥ እንደ አባታቸው ፈቃድ ለመኖር ራሳቸውን ይሰጡታል፤ ያስረክቡታል፤ ሮሜ 14÷7:8::
- ❖ ስለ ኾነም ምእመናን ልጆቹን የመምራቱና የመጠበቁ ኀላፊነት የእግዚአብሔር ይኾናል፤ ዮሐ. 6÷37-40:44፤ 10÷27-30፤ ሮሜ 8÷14፤ 1ቆሮ. 3÷16:17::

## 23.0 ወንጌልን አለመቀበል የሚያስከትለው ፍዳ

የሚሰበክላቸውን ወንጌል ለማመን ፈቃደኛ የማይኾኑት፥ በጌታችን ሞትና ትንሣኤ ከተገኘው በረከት ኹሉ ተካፋይ አይኾኑም:: ይልቁን እግዚአብሔር ፍቅሩንና ምሕረቱን ለኀጢአተኞች የገለጸበትን የአንድ ልጁን ስጦታ በማቃለላቸውና ማስተዛዘኛና አማራጭ የሌለውን የመጨረሻ ዕድል በመርገጣቸው፥ የእግዚአብሔር ቍጣ በላያቸው እንደ ኾነ ይኖራሉ፤ ማር. 12÷1-12፤ ዮሐ. 3÷18:36፤ 1ዮሐ. 5÷11:12::

## 24.0 መዳን በኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ለምን ኾነ?

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፥ «በሩ እኔ ነኝ፥ በኔ የሚገባ ይድናል፤» (ዮሐ. 10÷9) ብሏል:: ሐዋርያትም፥ «መዳንም በሌላ በማም የለም፥ እንድንበት ዘንድ የሚገባን፥ ለሰዎች የተሰጠ ስም ከሰማይ በታች ሌላ የለም፤» (የሐዋ. 4÷12) ብለዋል:: 'መዳን በጌታችን በኢየሱስ ክልርስቶስ ብቻ ለምን ኾነ?' የሚለውን ጥያቄ አበው በሚከተለው ኹኔታ አብራርተው መልስ ሰጥተውበታል: -

«ወአኮ ተስፋነ በሰብእ አላ በእግዚአብሔር እስመ ጽሑፍ ዘይብል ርጉም ዘይሴፈው ካልአ ዘእንበለ እግዚአብሔር ባሕቲቱ::

«ዘይሴፎ ዘከማሁ ሰብአ ይከውን ከመ ኪሄላ፤ ወናሁ ተከሥተ ለነ እስመ እግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ ኢኮነ ብእሴ ዕሩቀ እመለኮት ከመ ኵሉ ሰብእ እለ ዘከርናሆሙ ቅድመ፤ ወተዐውቀ ለኵሉ ሰብእ ከመ ንሕነ ንትአመን በእግዚእነ ክርስቶስ ከመ ውእቱ እግዚአብሔር ቃል ዘኮነ ሰብአ ዘእንበለ ኑፋቄ፤ ወኢኮነ ምትሐተ አላ በጽድቅ፥ ወአኮ ውእቱ ብእሲ ዘልሕቀ ወእምዝ ተጸገወ መለኮተ::

«ወኢኮነ ተስፋ መድኀኒትነ በሰብእ፤ ወኢክህለ ሰብእ ያድኅነነ እምአዳም እስከ ተፍጻሜተ ዓለም፤ አላ ውእቱ እግዚአብሔር ቃል ዘተሠገወ ከመ ኢይኩን ተስፋነ በሰብእ፥ ወኢንኩን ርጉማነ ወዳእሙ ተስፋነ በእግዚአብሔር ሕያው::

«ወሕይወትነሂ ኢኮነ በሰብእ፥ ወኢእምነትነ በሰብእ፥ እስመ ይቤ መጽሐፍ ይኩን ርጉመ ዘይትአመን በእጓለ እመሕያው::

«ወኢክህለ መኑሂ እምኵሉ ዘኮነ እምአዳም እስከ ይእዜ ይግበር መድኀኒተ ዘእንበለ እግዚአብሔር ቃል ከመ ኢይኩን ተስፋነ ሙሱነ እመ ኮነ በሰብእ አላ ለሊሁ አምላክ ጽድቅ ኮነ ሰብአ:: ... ከመ ኢይኩን ተስፋ ኵሉ ዓለም በሰብእ ረሰየ ትስብእቶ ይትወከፍ ሕማመ ከመ ይኩን ድኅነተ ዓለም በመለኮት ዘኢየሐምም:: -

«አለኝታችን እግዚአብሔር እንጂ ሰው አይደለም:: 'እግዚአብሔርን ብቻ እንጂ ሌላውን አለኝታ የሚያደርግ የተረገመ ነው' ተብሎ ተጽፎአልና (መዝ. 60÷11:12፤ 118÷5-9፤ 146÷3-5)::

«እንደ እርሱ ያለውን የተፈጠረ ሰው አለኝታ የሚያደርግ ኹሉ እንደ ፍሬ አልባ የበረሓ ዕንጨት ይኾናል (ኤር. 17÷5-8)፤ አለኝታችን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ግን፥ አስቀድመን እንደ ጠቀስናቸው ሰዎች ከመለኮት የተራቈተ ሰው ብቻ (ዕሩቅ ብእሲ) እንዳይደለ፥ እነሆ የተረዳ (የታወቀ) የተገለጠ ነው:: ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሰው የኾነ እግዚአብሔር ቃል እንደ ኾነ ያለመጠራጠር የምናምን መኾኑ ለሰው ኹሉ ታወቀ:: በምትሓት ሰው የኾነ አይደለም፤ በእውነት ሰው ኾነ እንጂ:: ካደገ በኋላ መለኮት ያደረበት ሰውም አይደለም::

«የመዳናችን አለኝታ በሰው አልተደረገም፤ ከአዳም ጀምሮ እስከ ዓለም ፍጻሜ ሰው ሊያድነን አልቻለም:: አለኝታችን የኾነውን ሕያው እግዚአብሔርን እንጂ ሰውን አለኝታ አድርገን እንዳንረገም ሰው የኾነው እግዚአብሔር ቃል አዳነን::

«መዳናችን በሰው እንዳልተፈጸመ፥ እምነታችንም በሰው አይደለም፤ መጽሐፍ 'በሰው የሚታመን የተረገመ ይኹን!' ብሏልና፤ ኤር. 17÷5-8::

«እግዚአብሔር ከኾነው ቃል በቀር ከአዳም ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ ከተፈጠረው ፍጥረት ኹሉ ማንም ማን ሊያድነን አልቻለም፤ አለኝታችን በሰው እንዳይኾንና ከንቱ እንዳይኾን ራሱ አምላክ ጽድቅ አዳነን እንጂ:: የሰው ኹሉ፥ የመዳኑ አለኝታ በሰው እንዳይኾን የዓለም ድኅነት ሕማም በሌለበት መለኮት ይኾን ዘንድ፥ መለኮት የተወሐደውን ሥጋውን መከራን እንዲቀበል አደረገ::» (ሃይ. አበው ዘኤጲፋንዮስ 58፤9÷9-12፤ 58፤13÷46:48:49:53)::

ከቅዱስ ኤጲፋንዮስ ማብራሪያ የምንጨብጣቸው ነጥቦች: -

1. እግዚአብሔር ወልድ ያድነን ዘንድ ሰው የኾነው፥ ከሰው ዘር መካከል አንዱ ሌላውን ሊያድን ባለመቻሉ ነው፤
2. 'በፍጡር የሚታመን፥ ተስፋ የሚያደርገውም ኹሉ የተረገመ ነው' ስለ ተባለ፥ ሰው ኾኖ ባዳነን በእግዚአብሔር ወልድ እንጂ በፍጡር እንዳንታመን፥ ያድነናል ብለንም ተስፋችንን በሰው ላይ እንዳናደርግና እንዳንረገም ነው፤
3. ባዳነን በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስንታመን፥ በሰው መታመናችን አይደለም፤ እርሱ ሰው የኾነ አምላክ እንጂ ሰው ብቻ አይደለምና፤

የሚሉት ናቸው።

## 25.0 ሰውን የማዳን ሥራ ተጠናቋል

ጌታችን አምላካችን መድኀኒታችን ኢየሱስ፥ ወደ ምድር የመጣበትን፥ በሞቱና በትንሣኤው ሰውን የማዳን ተልእኮውን ሊያጠናቅቅ ባለበት የመጨረሻ ቀን፥ «እኔ ላደርገው የሰጠኸኝን ሥራ ፈጽሜ በምድር አከበርሁህ፤ አሁንም አባት ሆይ! ዓለም ሳይፈጠር በአንተ ዘንድ በነበረኝ ክብር አንተ በራስህ ዘንድ አክብረኝ፤» አለ፤ ዮሐ. 17፥4:5:: በሞትና በሲዖል፥ በእነርሱም ላይ ሥልጣን ባለው በዲያብሎስ ላይ ድልን ከተቀዳጀ በኋላም በአብ ቀኝ (ዕሪና) ተቀምጧል:: ዛሬ ልዩ የኾነ ምስጋና በሰማይም በምድርም እየቀረበለት ነው፤ በሞቱ የሰውን ዕዳ የከፈለበት፥ በደሙ የኀጢአትን ስርየት የሰጠበትና የሰውን ዘር ከእግዚአብሔር ጋር ያስታረቀበት ውለታው፥ ለሚቀርብለት ምስጋና ዐቢይ ምንጭ ኾኗል፤ 1ጢሞ. 1፥15-17፤ ራእ. 1፥4-6፤ 5፥9-14::

የሚቀር ነገር ቢኖር በሰው በኩል ብቻ ነው፤ በየዘመኑ የሚነሡ ትውልዶች ከክርስቶስ ቤዛ መኾን የተነሣ ከታረቃቸው እግዚአብሔር ጋር ኹሉም ገና አልታረቁም:: ከእግዚአብሔር ጋር የታረቁ ኹሉ፥ ያልታረቁትን ወገኖች ከእግዚአብሔር ጋር እንዲታረቁ መጋበዝ ይጠበቅባቸዋል:: ሰዎች እምቢ እንታረቅም ካላሉ በቀር፥ እግዚአብሔር፥ ክርስቶስ በከፈለው ካሣ (ቤዛ) ምክንያት በበኩሉ መታረቁን ዐውጆ፥ የዕርቁን ሰነድ በደቀ መዛሙርት በኩል ለዓለም ልኳል፤ ማር. 16፥15:16፤ የሐዋ. 10፥42:43:: ወደ መቅደሱ የመግባት መብትንም ሰጥቷል፤ 2ቆሮ. 5፥18-21፤ ኤፌ. 2፥11-22፤ ቈላ. 1፥19:20፤ ዕብ. 10፥11-18::

ክብር፥ ምስጋና ውዳሴ የባሕርይ ገንዘቡ የኾነው አምላካችን፥ ከእርሱ ጋር ስታረቅ ሰው፥ መዳኑንና መታረቁን የሚያረጋግጡለትን ምስክሮች አቁሞለታል፤ እነዚህም: -

### 25.1 የእግዚአብሔር ቃል ምስክርነት

የልዑል እግዚአብሔር አንድዬ ልጅ፥ እስከ መስቀል ሞት ድረስ ሕይወቱን አሳልፎ የሰጠልን፥ ተምሳሊቱ በሕገ መሥዋዕት ሲሠራበት በነበረው መንገድ ለእኛ ተተክቶ ነውና፥ እንዲህ እንደ አደረገልን የምናምን ኹሉ መዳናችንን ምን ጊዜም እውነት ብቻ በሚናገርበት ቃሉ አረጋግጦልናል፤ ዮሐ. 3፥14-18፤ ሮሜ 3፥21-26፤ 4፥16-25::

### 25.2 የዐዲስ ኪዳን ሊቀ ካህናት መቀመጥ

የብሉይ ኪዳን ሊቃነ ካህናት ኹሉ፥ የሰማያዊት ቅድስተ ቅዱሳን ተምሳሊት ወደ ኾነችው ምድራዊት ቅድስተ ቅዱሳን በየዓመቱ በየሰሞናቸው ይገቡ የነበረው፥ አገልግለው ከዚያ ለመውጣት እንጂ በቅድስተ ቅዱሳን ይቀመጡ ዘንድ አልነበረም፤ ይህማ ከቶ አልተፈቀደላቸውም፤ ሥራቸው መቼ ተጠናቀቀና!!

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ግን፥ የዐዲስ ኪዳን ሊቀ ካህናት ኾኖ በምሥዋዐ መስቀል ላይ በፈሰሰው በራሱ ደም፥ ወደ ሰማያዊት ቅድስተ ቅዱሳን በገባ ጊዜ፥ ለኀጢአት ዘላለማዊ ስርየት ተገኘ፤ ዕብ. 9፥11:12:22-28:: ለሰው ዝግ የነበረችው ሰማያዊት ቅድስተ ቅዱሳንም ለምእመናን ተከፈተች:: ዘላለማዊ ስርየት በመስጠቱም፥ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሊቀ ካህናትነቱ ቆሞ ያገለግልበት ዘንድ የቀረ፥ ማለት ስርየት ያልተሰጠበት ኀጢአት ባለመኖሩም፥ አብ በቀኙ ይቀመጥ ዘንድ ጋበዘው፤ ተቀመጠ:: የሊቀ ካህናችን መቀመጥ ዘላለማዊ የኀጢአት ስርየት ለመስጠቱ (ለመገኘቱ) የሚያረጋግጥ ቋሚ ምስክር ነው፤ ዕብ. 7፥26:27፤ 10፥5-14::

### 25.3 የመንፈስ ቅዱስ ማረጋገጫ

ቃለ ወንጌልን፥ ወይም በወንጌል ላይ የተመሠረተ ስብከትን ስንሰማ፥ ወይም ስናስብ፥ እግዚአብሔር እንቀበለው ዘንድ የላከልን መልእክት ነው ብለን አምነን ልንጠቀምበት የምንችለው፥ እንደ ልድያ መንፈስ ቅዱስ ልባችንን ሲከፍትልን ነው፤ የሐዋ. 16፥14:15::

በመንፈስ ቅዱስ አብርሆት ካልተገለጸልን በቀር፥ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አንድ ጊዜ መሥዋዕት አድርጎ ራሱን በማቅረቡ፥ ዘላለማዊ ስርየት የመገኘቱና በዐዲስ ኪዳን ሊቀ ካህናት መቀመጥ፥ ይቀርብ ዘንድ የሚያስፈልግ ተጨማሪ ወይም ሌላ የኀጢአት ስርየት መጠየቂያ መሥዋዕት የለም የመባሉ ትርጒም ከቶ አይገባንም፤ ስለማይገባንም ቃሉን ተቀብለን፥ ከራሳችን ጋር በእምነት ልናዋሕደው አንችልም:: በዚህና በመሳሰለው ኹሉ፥ የመንፈስ ቅዱስ ምስክርነት ታላቅ ስፍራ አለው፤ ዮሐ. 15፥26:27፤ ዕብ. 9፥6-14፤ 10፥15-18::

ወደ ገጽ 26 ዞሯል

የጮራ መጽሔት ማኅበረተኛ መኾን የምትፈልጉ በመ.ሣ.ቁ. 23956 ከድ 1000 የሦስት መጽሔት ዋጋ እስከ መላኪያው ብር 16.00 ብትልኩ በአድራሻችሁ እንልካለን:: ይህ ማስታወቂያ ለአገር ውስጥ ማኅበረተኞች ብቻ ነው::

# አለቃ ነቅዐ ጥበብና አገልግሎታቸው

## ትረካ፡ - ከነቅዐ ጥበብ

የዘንድሮው የዘመን መለወጫ በዓል ከምእመናን የሚቀርቡ ጥያቄዎች ምላሽ የሚያገኙበት፥ «የጥያቄና መልስ ቀን» እንዲኾን በተወሰነው መሠረት መስከረም 1 ቀን በበዓለ ቅዱስ ዮሐንስ መጥምቅ፥ ብፁዓን አበው፥ ንዑዳን ምእመናንና ትጉሃን የዕለተ እሑድ ትምህርት ተከታታዮች፥ በዚህ ተወዳጅ ፕሮግራም ላይ ለመገኘት በደብረ ኢጲፋንዮስ ተሰብስበው ነበር።

ጉባኤውን በጸሎት የከፈቱት፥ በአግዐዝያን አብያተ ክርስቲያናት ሊቀ ጳጳሳት ስም ብፁዕ አቡነ በትረ ሃይማኖት ነበሩ። ብፅዑነታቸው መዝሙረ ዳዊት 42፥1-5 (ዐ.መ.ት.) እንብበው ትምህርት ሰጥተዋል። እንዲህም አሉ፥ «መዝሙረ ዳዊት ከጠቅላላው የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት መካከል መዝሙራት ተብለው ከሚጠሩት የቅኔ መጻሕፍት ጋር ይመደባል። በዝማሬ፥ በውዳሴ፥ በስብሐት፥ በጸሎት፥ በምልጃ ቅዱሳን አባቶቻችን ሲቀኙበት ኖረው፥ ለእኛ ለዛሬው ዘመን ትውልድ አስረክበዋል።

«በሀገራችን ፊደል ከመቍጠር የሚጀምሩት ወጣቶች ዳዊትን በጥሩ ኹኔታ በግእዝ ማንበብ ከቻሉ፥ 'ዳዊት ደገሙ' ተብሎና በትምህርታቸው አንድ እርከን እንደ ወጡ ተቈጥሮላቸው ይሸለሙ ነበር።

«ከዚያ በኋላ በቋንቋቸው ትርጕሙን ባያውቁትም ተማሪዎቹ፥ ከሃያ እስከ ሠላሳ መዝሙራትን በዚያው በተማሩበት ቋንቋ በግእዝ፥ ሲያነብቡ ያው እንደ ጸሎቱ እየተቈጠረላቸው 'ዳዊት ደጋሚ ናቸው' ያሰብላቸው ነበር።

«ቅዱስ ያሬድ ግን ንባቡን ከነትርጕሙ፥ ደግሞም ከነምስጢሩ የተረዳ ስለ ነበር፥ እግዚአብሔር ይመሰገንበት ዘንድ ያዘጋጀውን የዜማ ድርሰቱን ከዚሁ ከዳዊት መዝሙር ውስጥ ለዝግጅቱ ተስማሚ የኾኑ ንባቦችን እየጠቀሰ፥ ከሌሎቹ የብሉይና የሐዲስ ኪዳን ቃላት ጋር፥ እንደ ዕንቍ ፈርጥ በማሰባቀልና በመሰገጥ የንባብና የታሪክ፥ የምስጢርም ውበት እንዲያገኙ አድርጓቸዋል። ቀድሞም በብሉይ ኪዳኑ ቤተ መቅደስ፥ ከዐሥራ ኹለቱ አንጋደ እስራኤል፥ ሌዊ ለመንፈሳዊ አገልግሎት የተመረጠ በመኾኑ፥ ከሌዊ ልጆች መካከልም አሮንና ልጆቹ ካህናት ተብለው ለመሥዋዕት አቅርቦት ሲመደቡ፥ ሌሎቹ የሌዊ ልጆች ሌዋውያን ተብለው የካህናቱ ተራዳእያን ኾነው ከቤተ መቅደሱ ጋር የተያያዙ የተለያዩ አገልግሎቶችን ያከናውኑ ነበር።

«በተለይም የእግዚአብሔርን ጉባኤ በጸሎትና በውዳሴ፥ በማሕሌትም የሚመሩት እነዚሁ ሌዋውያን ስለ ነበሩ፥ በዳዊት ስም ከሚታወቀው መዝሙር ለወቅታዊ በዓል ተስማሚ የኾነውን በዜማ፥ በኀብረትና በማስተዛዘል ይዘምሩ (ይቀኙ) ነበር፤ ዝማሬያቸው የዜማ ምልክቶችን (ኖታዎችን) ተከትሎ እንደየኹኔታው በመሰንቆ፥ በበገና፥ በጸናጽል፥ በመለከት ይታጀብ ነበር፤ 1ዜና. 6፥1-48፤ 16-4-37።

«ሌዋውያን እንደ ሌሎቹ አንጋደ እስራኤል ርስት ባይደለደልላቸውም፥ ከየነገዱ ርስት የተቀነሱ 48 ከተሞች ለማረፊያ የተሰጣቸው ሲኾን ለኑሮአቸውም ከወንድሞቻቸው ዐሥራት የመቀበል መብት በሕግ ተደንግጎላቸው ነበር፤ ዘኍ. 18፥20-32። ዋናው ርስታቸው መኖሪያቸው ስብሐተ እግዚአብሔር ነበር።

«ለትምህርት ያቀረብነውን ይህ መዝሙር የተቀኘው በስደት ላይ የነበረ ሌዋዊ እንደ ኾነ ለመዝሙሩ ከተሰጠው ርእስ መረዳት ይቻላል።

### «1.0 ሌዋዊ በምን ምክንያት ይሰደዳል?

«በክብሩ ገናና፥ ብቻውንም ፈጣሪ ሰማያት ወምድር የኾነውን የአባቶቹን አምላክ እግዚአብሔርን በስድ ንባብ ቅኔና ባማረ ዜማ የሚያወድስበትን ማሕሌተ እግዚአብሔርን እየተመገበ የሚኖርበትን ተወዳጅ አገልግሎቱን ትቶ ሌዋዊ ለምን ይሰደዳል? ወዴትስ ይሄዳል? ዛሬ እንደሚኾነው ኹሉ ያን ጊዜም እውነተኞች የእግዚአብሔር አገልጋዮች የሚሰደዱባቸው ብዙ ምክንያቶች ሊኖሩ እንደሚችሉ አይጠረጠርም። 'በእውነትም ... እግዚአብሔርን እየመሰሉ ሊኖሩ የሚወዱ ኹሉ ይሰደዳሉ፤' 2ጢሞ. 3፥12።

### «1.1 በአምልኮተ እግዚአብሔር መበረዝ ምክንያት ይሰደዳል

«'በምድር ላይ እንደ ተፈተነ፥ ሰባት ጊዜ እንደ ተጣራ ብር የእግዚአብሔር ቃላት የነጹ ናቸው፤' ያለው ዘማሪው ዳዊት ነው፤ መዝ. 12፥6። ንጹሕና ጽሩይ በኾነው በእግዚአብሔር ቃል ላይ የተመሠረተውን ንጹሑን አምልኮተ እግዚአብሔር የሚበክሉ፥ ጕድፍ አስተምህሮዎች፥ እንደ ሸቀጥ ከጎረቤት ወይም በሰይጣን ከተቃኘ የሰው አእምሮ ጕሥዐተ ልብ (ልብ ወለድ) ኾነው ወደ ቤተ እግዚአብሔር ሲገቡ፥ የእግዚአብሔርን ክብር የሚሻማውን ሥርዐተ አምልኮ አንመራም፥ ወይም አንሳተፍም ሲሉ በግል ውሳኔአቸው፥

ጋር አመሳስሎታል፤ ያን ያህል ነፍሱ አምላኳን ተጠምታ ነበርና።

«ሳይኾኑ አማልክት ናቸው የተባሉና አማልክት የተደረጉ ጣዖታት በስደቱ ምድር ነበሩ። ቢማጸኗቸው ተስፋ ይኾናሉ የተባሉ የብዙ መናፍስት ስሞች ሌዋዊው በተሰደደበት ሀገር መቼ ጠፉ! ቢጠሯቸው፥ ቢለምኗቸው ረድኤት ይኾናሉ የተባሉ የሙታን ነፍሳትስ ምድሪቱን ሞልተው አልነበረምን? እነዚህ ኹሉ ንጹሕና እውነተኛ አምልኮተ እግዚአብሔር ለተለማመደው ሌዋዊ ምኑም አይደሉም። እነዚህ ኹሉ የውሃ ወለድ በሽታ ፈጣሪ በኾኑ ረቂቃን ተሐዋስያን የተሞሉ ምንጮች ዐይነት ናቸው። ለሌዋዊው የሕይወቱ ውሃ ምንጭ ያህዌ የኾነው አምላኩ ብቻ ነውና። ከእርሱ ጋር የሚገናኝበት ዕድሉ እስከሚለቀቅለት ድረስ የነፍሱ ጥማት እየጨመረ መሄዱ የታመነ ጉዳይ ነበረ። ያን ዕድል እንደ ገና የሚያገኝበት ተስፋ ያለው ቢኾንም፥ ጊዜው ስለ ራቀበት፥ 'መቼ ነው የአምላኬን ፊት የማየው?' አለ። ወደ አምላኩ ቀርቦ ፊቱን ለማየት ናፈቀ፤ እንደ ዳዊት፥ 'እኔ ግን በጽድቅ ፊትህን አያለሁ፤ ክብርህን ሳይ እጠግባለሁ፤' (መዝ. 17፥15) የሚል ሰው ነውና።

**«3.0 የቤተ እግዚአብሔር ትዝታ በስደት ይብሳል**

*ታላቅ ሕዝብ ወደ እግዚአብሔር ቤት እየመራሁ፥ በእልልታና በምስጋና መዝሙር፥ በአእላፍ ሕዝብ መካከል እንዴት ከሕዝቡ ጋር እሄድ እንደ ነበር ትዝ አለኝ፤ መዝ. 42፥3:4።*

«ስደተኛው ሌዋዊ የአምላኩን ፊት ይበልጥ እንዲጠማ ያደረጉት፥ ወይም ጥማቱን ያባባሱበት ጠላቶቹ ነበሩ። የአባቶቹን አምላክ ያህዌን ስሙን እየጠሩ፥ 'አምላክህ የታለ? አምላክህ ካንተ ጋር የመኖሩ ምልክት ምንድን ነው? በስደት ኾነህ እየተቸገርህ አይደለምን?' እያሉ ያለማቋረጥ ሲነዘንዙት፥ ነፍሱ ከመጨነቋ የተነሣ እየቈዘመች ነበረች።

3.1 በቀድሞዎቹ ዓመታት ተትረፍርፎለት የነበረውን የአምላኩን ባርኮት ነፍሱ አስታወሰች። ባለፉት ቅርብ ዓመታት በክብረ በዓላት፥ ጥንድ ድርቡን ለብሶ ወደ እግዚአብሔር ጉባኤ የሚመጡ ተሳላሚዎችን በከተማው አደባባይ ተቀብሎ በዝማሬ ቅኝት እየመራቸው፥ የቤተ መቅደሱን ዐውደ ምሕረት እያቋረጠ ደረጃዎችን ይወጣ የነበረበት ጊዜ ትዝታው መጣበት። እርሱ እየቀደመ የክብረ በዓሉን ተገቢ መዝሙር ሲቃኝ፥ የተከተሉት ምእመናን ዝማሬውን ሲቀበሉና ሲቀባበሉ፥ አየራትን ሰንጥቆ በጽርሐ አርያም ያስተጋባ የሚመስለው የዜማቸው ድምፅ፥ ዛሬ እንኳ በስደት ምድር ነፍሱ ከማስታወስ በላይ አሁን እየኾነ እንዳለ፥ ድምፁ በጆሮው ያስተጋባል፤ መዝ. 122፥1-9።

3.2 ሌዋዊው ይህን ኹሉ ማጣቱ ሳያንሰው፥ 'ያንተ መመኪያ አምላክህ የታለ?' ሲሉት ቀኑንና ሌሊቱን በእንባ መታጠቡን ሥራዬ ብሎ ተያያዘው። በልቅሶ እጉርጉሮ ውስጥ እያለ: -

**«4.0 ተስፋ እንዳለው ተስማው**

'ነፍሴ ሆይ ለምን ትተክዢያለሽ? ለምንስ በውስጤ ትታወኪያለሽ? ተስፋሽን በአምላክ ላይ አድርጊ፤ አዳኜንና አምላኬን ገና አመሰግነዋለሁና።' (መዝ. 42፥5) ይል ዘንድ ተበረታታ።

«ስደተኛው ሌዋዊ ሌሊቱንና ቀኑን በእንባ እየታጠበ ባለበት ጊዜ፥ የሚያጽናና ቃል ነፍሱ ተቀበለች። እርሱም ነፍሱን 'አይዞሽ ተረጋጊ፤ አምላኬን አመሰግነው ዘንድ ገና ዕድል ፈንታ አለኝና በውስጤ ኾነሽ አትታወኪ' አላት።

«ሌዋውያን በምድራቸው ኾነው፥ ወይም ተሰደው በሀገራቸው የሚታየውን የተዘበራረቀ ነገር ሲመለከቱ፥ ልባቸው በሐዘን ቢሞላ፥ ቢያነቡ አያስደንቅም። ሊኾን የሚገባው የንስሓ ሐዘን ነው። የተባለውና ያልተባለው ችግር ይመጣ ዘንድ እነርሱም አስተዋፅኦ ማድረጋቸው አልቀረምና። እነርሱ ቀድመው በእግዚአብሔር ፊት መውደቅና ስለ ራሳቸውና ስለ ሕዝቡ ኀጢአት ንስሓ ሊገቡ ያስፈልጋቸዋል። ከእግዚአብሔር ጋር የታረቁ ሌዋውያን ናቸው ሕዝቡን ከእግዚአብሔር ጋር ማስታረቅ የሚችሉት።

«ስደተኛው ሌዋዊስ ለጸሎቱ፥ ለእንባው፥ ለምሕላው መልስ አገኘ፤ ከአምላኩ ጋር ኅብረት ለማድረግ ተስፋ እንዳለው ስለ ተረዳ ተጽናና። በመንፈስ ወይም በሥጋ ስደተኞች የኾኑ ኢትዮጵያውን ሌዋውያንስ ከዚህ ምን ይማራሉ?

«ታሪክ እንደሚለን፥ ኢትዮጵያውያን አበው በእግዚአብሔር በረከት ውስጥ የዋኙባቸው የቀድሞዎቹ ዓመታት ትዝታዎች እንዲህ በቀላሉ የሚረሱ አይደሉም።

- ለጥበብ ማወዳደሪያ ተደርጎ በመጽሐፍ ቅዱስ የተጠቀሰው የከበረ ዕንቍ፥ 'ቶጳዝዮን' ይገኝ የነበረው በኢትዮጵያ ነበር፤ ኢዮ. 28፥19።
- ንግሥተ ሳባ በግመሎች አስጭና ወደ ኢየሩሳሌም ያጓጓዘቻቸው
  - የሽቱ ብዛት
  - እጅግ ብዙ የተባለ ወርቅና
  - የከበሩ ዕንቍዎች

  በሰሎሞን ቤተ መንግሥት ኢትዮጵያን ያስደነቁ ስጦታዎች ነበሩ፤ 1ነገ. 10፥1-10
- በቀይ ባሕር በሚከንፉና በሚሰፍፉ የንግድና የባሕር ኀይል ሰራዊትና

መርከቦቿ፥ ነቢዩ ኢሳይያስ በነበረበት ዘመን ታዋቂ የነበረች ሀገር ጥሩ ቢባል ኢትዮጵያ ቊጥር አንድ ትኾናለች፤ ኢሳ. 18፥1::

- ❖ ወደ መካከለኛው ምሥራቅ ግብጽንና ሊቢያን በማስተባበር፥ እየዘመተ ያጠቃ የነበረ ሰራዊት የነበራት አፍሪካዊት ሀገር ማናት ቢባል፥ ኢትዮጵያ ነች፤ 2ነገ. 19፥9፤ 2ዜና. 12፥3-9፤ 14፥9-15::
- ❖ እስከ መካከለኛው ምሥራቅ የጦር ኀይሉን በሚያዘምተው በኑቢያ መንግሥት ሰራዊት ውስጥ፥ እንደ ግብጽ ታላቋ ተባባሪና መሪ የተባለች በታሪክ የምትታወቅ ኢትዮጵያ ነበረች፤ ናሆ. 3፥8-9::
- ❖ ኢትዮጵያ ጥቅጥቅ ባሉ ደን ለበስ በኾኑ ሸለቆዎቿና ተራራዎቿ፥ ሰማይ ጠቀስ በኾኑ ዛፎቿና በደኖቿ ውስጥ በሚርመሰመሱ የዱር እንስሳዎቿ ታዋቂ እንደ ነበረች የቅርብ ጊዜ ትዝታ ነው::
- ❖ ለጎብኚዎች ዐይን መስሕብ የኾኑ የአክሱም ሐውልቶቿና የላሊበላ ሕንጻዎች ዛሬም አሉ::
- ❖ በመንፈሳዊው የታሪክ ጕዞ እግዚአብሔር፥ 'እናንተ እስራኤላውያን ለእኔ እንደ ኢትዮጵያውያን አይደላችሁምን?' ተብሎልናል፤ አሞ. 9፥7::
- ❖ የጌታን የኢየሱስ ክርስቶስን የማዳኑን የምሥራች የያዘው ወንጌል፥ ከምድረ እስራኤል ውጪ ከሰማርያ ቀጥሎ የተሰበከው ለኢትዮጵያ ነበር፤ የሐዋ. 8፥26-40::

«በመጽሐፍ ቅዱስ ወተትና ማር የምታፈስ ምድር ያላት ሀገር የተባለችው ሌላ ብትኾንም፥ ከእርሷ ባልተናነሰ ኹኔታ ለምለምነትን በተፈጥሮ የታደለች ኢትዮጵያ በታሪክ ነበረች::

«እስራኤል ወተትና ማር የምታፈስስ መኾኗ ቀርቶ፥ እሾኽና አሜከላ በበቀሉባትና ነጻነቷን ዐጥታ በነበረ ጊዜ፥ ሀገራቸውን እየተዉ የተሰደዱ፥ ሳይሰደዱም በገዛ ሀገራቸው ስደተኛ የኾኑ ሌዋውያን የቀድሞውንና የኋለኛውን ባስታወሱ ቊጥር ዐይኖቻቸው በእንባ ተሞሉ፤ (ሰቈቃወ ኤርምያስ)::

«ስለ ኾነም አልቃሻውን ሌዋዊ የእግዚአብሔር መንፈስ አነቃቃው፤ ከተስፋ መቊረጥ አውጥቶ በተትረፈረፈ ተስፋ ሞላው፤ ትንቢትንም በአፉ አቀበለው፤ ያለፈው መልካም ነገር ኹሉ 'ነበር' ኾኖ እንደማይቀር፥ ከእግዚአብሔር ጋር ያለው ኅብረት እንደሚታደስ፥ የእስራኤል አምላክ ምስጋና እንደ ገና ልቡን ሞልቶ በአፉ እንደሚፈስስ ነገረው:: ስለ ኾነም ነፍሱ እንደትረጋጋና በአምላኳ ላይ የተመሠረተውን ተስፋዋን እንድታጸና መከራት::

«ይህ ዕድል ለእኛ ይመጣል ወይ? መቼ? በመዝሙር 68፥31 እንደ ተነገረው፥ የእግዚአብሔርን ድል አድራጊነት ኢትዮጵያ ስትቀበል፥ እጆቿን ወደ ላይ በማንሣት 'ከእንግዲህ ወዲህ ለአንተ ተማርኬአለሁ' ስትል፥ ዐይኖቿን ከተራሮች ላይ በማንሣት መንፈስ የኾነውን እግዚአብሔርን ማየት ስትጀምር፥ ጆሮዎቿም ለእርሱ ቃል ብቻ ሲከፈቱ የጸሎት፥ የምልጃ፥ የምስጋና፥ የትንቢት መንፈስ ይፈስስልናል::

«ያን ጊዜ ጨኸት የኾነ የሥጋ ቀረርቶ ይቀርና፥ 'አእኰተከ አብ ... በዝ ቃል ዘበላዕሌነ መንፈስ፤ - በላያችን ከፈሰሰው መንፈስ ቅዱስ በሚመነጭ ልሣን፥ አብ ሆይ አመሰግንሃለሁ' የሚል ወደ ጸባዖት ጆሮ የሚደርስ ዝማሬ ይንቈረቈራል:: በሥጋና በደም የሚገዘገዘው መሰንቆና የሚከረከረው ክራር በገና ኖሩም አልኖሩም፥ በመንፈስ ቅዱስ በተቃኘ ልብ የሚፍለቀለቅ አርያማዊ ዜማ በጽርሐ አርያም ያስተጋባል::

«በምስክርነታቸው እንደ ደመና በዙሪያችን ከከበቡን ቅዱሳን ምስጋና ጋር አብሮ የሚሰማ ምስጋና፥ የብዙ ውሆች ክምችት እንደ ፈጠረው ጕርፍ የጌታን ዙፋን ይከብባል፤ ራእ. 5፥8:: ጌታ ሆይ! አሁን በኢትዮጵያ ይህ ይኾናልን?» በማለት አቡኑ ትምህርቱን ጨረሱ::

ከዚህ ቀጥሎ እያንዳንዱ የጉባኤው ተሳታፊ፥ ምስጢሩ የጸነነበትን (ግልጽ ያልኾነለትን) ጥቅስ እየተናገረ በትርጓሜ እንዲብራራለት ጠይቆ የሚረዳበት ዕለት ኾኖ መመደቡን በማስታወስ፥ ጥያቄዎችን በየተራ እየተቀበሉ እንዲመልሱ የተጋበዙት: -

- ⇨ አለቃ ነቅዐ ጥበብ
- ⇨ መምህርት ሲያዴ
- ⇨ ርእሰ ደብር ደምፀ

በተዘጋጀላቸው ስፍራ ተቀመጡ:: እንደ መክፈቻም አለቃ ነቅዐ ጥበብ እንዲህ ሲሉ ተናገሩ::

«ቀድሞ በቤተ ክርስቲያናችን የተጠየቀ፥ ልጠይቅህ ልምድ ነጻ ዕውቀት በገፍ የሚሸመትበት ትልቁ የገበያ ማእከል እንደ ነበር አበው ይተርካሉ:: ቅኔ ተቀኝቶ ሳይጠየቅና ሳያስረዳ ማንም ቢኾን ሊያመልጥ ከቶ አይችልም ነበር:: ሰባኪውም፥ መጽሐፍ ተርጓሚውም እንዳሰኘው ተናግሮ ሹልክ ብሎ ለመሄድ ፈጽሞ የማይሞከር ነበር::

«ቅኔውን፥ ስብከቱን ወይም ትርጓሜውን ያዳመጡ መምህራንና ደቀ መዛሙርት፥ 'አያሰኝም፥ አያስኬድም' የሚሉት ከኾነማ እንደ ገና፥ 'አይዋ፥ እስኪ ይምጡ፤ በዚህ ላይ አረፍ ይበሉ' ይሉታል:: አንዱ ደቀ መዝሙር የለበሰውን ደበሎ አንጥፎለትና እመኻል ተቀምጦ በተቀኘው፥ በሰበከው፥ በተረጐመው ላይ ተመሥርተው የሚቀርቡለትን ጥያቄዎች አንድ በአንድ መመለስ ግዴታው

ምን ይበል? ኖኅና በእርሱ ዘመን የነበሩት እኛንና ከእኛ በኋላ የሚመጡትን ይጠብቃሉና ምን ይበሉ? ወንድሞች ሆይ! ከእነርሱ ይልቅ እኛ እንደምንከብር ዐወቃችሁን? እግዚአብሔር አስቀድሞ ስለ እኛ የሚበልጥ ነገርን አይቷልና:: እኛን በተጋድሎ የቀደሙት ከእኛ በፊት አክሊል የተቀበሉ ለማንም እንዳይመስለው ለኹሉም አክሊል መቀበያ የሚኾን አንድን ጊዜ ወስኗል:: እነሆ ከቀድሞ ጀምሮ ተጋድሎአቸውን በመፈጸም ድል አድራጊ የኾኑት፥ እኛ እስክንሄድ ድረስ ይህን ያህል ዘመን አክሊል አላገኙም:: ... በተጋድሎ ቀድመውናል፤ ነገር ግን አክሊል በመቀበል አልቀደሙንም::' (28ኛ ድርሳን ቍጥር 34-72)::

«የገድልን፥ የድርሳንን፥ የተኣምርንም በጠቅላላው የአዋልድ መጻሕፍትን ነገር ካነሣነው፥ 'ከእውነተኞቹ ሐሰተኞቹ ይበዛሉ' መባላቸውን ልንረሳ አይገባንም፤ (ወዳጅ ልቤ ገጽ 54፤ ከብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደ ሥላሴ 1963 ዓ.ም.)::

«ኾኖም እውነትን ለማመን ፈቃደኞች ባለመኾናቸው ፍርድን ይቀበሉ ዘንድ፥ የእውነትን ተቃራኒ ሐሰትን እንዲያምኑ እግዚአብሔር የስሕተትን አሠራር ለላከባቸው ኹሉ ይህ ከማስተዋላቸው በላይ ነው፤ 2ተሰ. 2፥11:12::

**ጥያቄ: -** ከአባ ይልቃል ምሕረቱ

«ጌታ በተሰቀለበት መስቀል አጠገብ ቆመው ከነበሩት መካከል፥ እናቱንና ይወደው የነበረውን ደቀ መዝሙር ዮሐንስን አያቸውና፥ እናቱን፥ 'አንቺ ሴት እነሆ ልጅሽ አላት፤ ዮሐንስንም እናትህ እነኋት አለው' የሚለውን ቃለ ወንጌል መምህራችን እንደሚከተለው ተርጕመው አስተማሩን::

«'ዮሐንስ በመስቀሉ አጠገብ የተገኘው፥ ምእመናንን ኹሉ ወይም ቤተ ክርስቲያንን ወክሎ ነውና፥ 'አንቺ ሴት እነሆ ልጅሽ' ብሎ ጌታ ለቅድስት ድንግል ማርያም መናገሩ፥ ምእመናን ልጆችሽ ይኹኑ ሲላት ነው፤ ለዮሐንስም፥ 'እናትህ እነኋት' ማለቱ፥ 'እናንተም ምእመናን እናቴ እናታችሁ ናት፥ እናት ትኹንላችሁ ማለቱ ነው' ብለውናል::

«በዚህ ዐውደ ንባብ ውስጥም ኾነ በሌላ ምንባብ ውስጥ፥ ዮሐንስ ቤተ ክርስቲያንን ወክሎ የተነገረበት፥ ቤተ ክርስቲያንም ለማርያም ዐደራ የተሰጠችበት ስፍራ አላጋጠመኝም:: ይህን ዐይነቱን ሥነ ትርጓሜ ከቃሉ ጋር እንዴት ልናዛምደው እንችላለን?»

**መልስ: -** ከአለቃ ነቅዐ ጥበብ

«ሰይፈ ገብርኤል እባላለሁ ያሉ ወንድምም፥ ለመጽሔታችን የጥያቄ ዐምድ በደብዳቤ የላኩት ጥያቄ ከዚህ ጋር ይመሳሰላል:: እስኪ ምላሹን ወደ መስጠት እንሂድ::

«1.0 በመስቀሉ አጠገብ ቆመው የነበሩት፥

- ⇨ ቅድስት ድንግል ማርያም፥ የጌታ እናት፥
- ⇨ ዮሐንስ፥ ጌታ የሚወደው ደቀ መዝሙር፥
- ⇨ የጌታ የእናቱ እኅት፥
- ⇨ ማርያም የቀለዮጳ ሚስት፥
- ⇨ መግደላዊት ማርያም

እነዚህ ዐምስቱ ሲኾኑ፥ ጌታ ግን ኹለቱን፥ ማለት እናቱንና ዮሐንስን ብቻ ለይቶ አናገራቸው፤ ይህ ማለት ንግግሩ በቀጥታ ኹለቱን ብቻ የሚመለከት ነው፤ ከኹለቱ ውጪ ማንንም አይጨምርም::

«2.0 ልጆችሽ ይኹኑ ለማለት ቢፈልግ ኖሮ፥ ከዮሐንስ ጋር አብረው የነበሩትን የእናቱን እኅት፥ የቀለዮጳን ሚስት፥ መግደላዊት ማርያምን ጨምሮ እነዚህ ልጆችሽ ይኹኑ ሲል በተናገረ ነበረ:: እነዚህ ኹሉ ከሌሎች ብዙኃት ሴቶች ጋር፥ ጌታን ሲከተሉትና ሲያገለግሉት እንደ ነበሩና (ሉቃ. 8፥2:3) እንደ ዮሐንስ እነርሱም እስከ መጨረሻው ሰዓት ድረስ ከጌታ ያልተለዩ፥ የመጀመሪያዪቱ ቤተ ክርስቲያን አባላት እንደ ኾኑ ጠቋሚ ጥቅሶች አሉ፤ (ሉቃ. 23፥49፤ የሐዋ. 1፥12-14)፤ ጌታችን እነዚህን ኹሉ ከንግግሩ ውጪ አደረገና፥ እናቱን የመንከባከቡን ዐደራ ለዮሐንስ ብቻ ሰጠው::

«3.0 ሌሎች ሴቶች ባለትዳር ነበሩ፥ ውድ እናቱን እንደሚገባት ሊንከባከቧት፥ ሊያገለግሏት ስለማይችሉ እርሷን የመንከባከቡን ኀላፊነት ላላገባው ለዮሐንስ ሰጠ፤ ስለዚህም ነው ዮሐንስ ከዚያች ሰዓት ጀምሮ ወደ ቤቱ የወሰዳት::

«4.0 ሰይፈ ገብርኤል እንደ ተረዱትና እንዳስረዱን፥ 'እኛንና እናንተን ሥነ ትርጓሜ ይለየናል' ባይ ናቸው:: ያልተጻፈ ከሚያነብቡ፥ ያልተነበበም ከሚተረጕሙ ክፍሎች መለየት፥ ለእኛ ትርጕምና አግባብነት እንዳለው እናምናለን፤ መታደልም ነው:: 'በመጽሐፍ ያለውን ትንቢት ኹሉ ማንም ለገዛ ራሱ ሊተረጕመው አልተፈቀደም፤ ትንቢት ከቶ በሰው ፈቃድ አልመጣምና፤' 2ጴጥ. 1፥21::

«5.0 እነ ሰይፈ ገብርኤል በሚከተሉት ስድና ልቅ ሥነ ትርጓሜ መመራት ካለ፥ 'ዮሐንስ ወንድሜን ይወክላል፥ ማርያም እክስቴን ትወክላለች' እስከ ማለት ያደርሳልና ለዚህ መፍትሔው ዐውዱ በሚሰጠው ሐሳብ መወሰን ነው::

«አንድ ጊዜ ይህንኑ ክፍል አንድ ሰባኪ በተለየ መንገድ ሲተረጕመውና ሲሰብከው ነበር፤ 'የጌታ እናት የተገኘችው ከሌሎች ሦስት ሴቶች ጋር ነበር፤ ከነዚያ ሴቶች መካከል እናቱን ለይቶ ለዮሐንስ እናትህ እነኋት አለው:: እናቱ የዐዲስ ኪዳን ምሳሌ ናት፤ ዐዲስ ኪዳንን ጠብቅ ታድንሃለች ሲለው ነው:: ሌሎቹ ሦስቱ ሴቶች የብሉይ ኪዳን ምሳሌዎች ናቸው፤ ሕግ፥ ነቢያት፥ መዝሙራት ተብለው በሦስት ክፍሎች ይታወቃሉና (ሉቃ. 24፥44) ብሉያት ወደ ዐዲስ

ኪዳን ከሚያደርሱህ በቀር አያድኑህም፥ እነርሱን ዕለፋቸው፤ በምታድንህ በዐዲስ ኪዳን ላይ ትኵረት አድርግ ሲለው ነው፤' አለ። ምን ይደረግ ኹሉም የእግዚአብሔርን ቃል እየመዘዘ፥ ለሚወዳቸው ለመስጠት ሲል ከዐውዱ ውጪ ለመተርጐም በራሱ መንገድ ፋነነ፤ ኢሳ. 53፥6። እርሷን ዮሐንስ እንደ እናቱ እንዲንከባከባት ዐደራ ተሰጠችው እንጂ፥ ዮሐንስ ለማርያም አልተሰጠም። እንደዚያማ ቢኾን እርሷ ትወስደው ነበር እንጂ፥ መቼ እርሱ ወደ ቤቱ ይወስዳት ነበር።

«6.0 ከሟች የአዳም ልጆች መካከል ከተገኘችው እናቱ ይልቅ፥ እጅግ ለሚበልጠው ለእኀዜ ዓለም፥ ኹሉ ለሚቻለው፥ አንዳች ለማይሳነው ለልዑል አባቱ ምእመናንን ዐደራ አስጠብቋቸው የለምን? ይህ ነው የምሥራች የሚያሰኘው ቱስፋ!! ዮሐ. 17፥9-26። የቅዱሳን ጸሎትም፥ 'አብ ሆይ! ስለ ኢየሱስ ብለህ ርዳን፥ ክርስቶስ ሆይ ወደ አባትህ ዐደራ አስጠብቀን፤ የአብና የወልድ መንፈስ ሆይ! አጽናናን' የሚል ነበር። ለፈጣሬ ሰማያት ወምድር ዐደራ ከሰጠን በኋላ፥ ከእርሱ ነጥቆ ከምእመናን አንዷ ለኾነችው እንዴት ዐደራ ይሰጠናል?

«ቅድስት ድንግል ማርያም፥ ፈጣሪዋን እግዚአብሔር ወልድን በሥጋ መውለዷ በመንፈስ የተቃኙ ቅዱሳን በጻፉት መጽሐፍ፥ 'የኢየሱስ እናት' አሰኝቶአታል፤ ዮሐ. 2፥1፤ የሐዋ. 1፥14። ኢየሱስ መባልም ለሥግው ቃል የተሰጠ ስም ነው፤ ማቴ. 1፥21፤ ሉቃ. 1፥31።

«ቅድስት ድንግል ማርያም፥ በልደተ ሥጋ እናቱ ትኾን ዘንድ መመረጧ፥ 'እም ወአመት - እናትም አገልጋይም' አሰኛት እንጂ (ሉቃ. 1፥38) ባሕርየ ተፈጥሮዋን ለውጦ ለሥላሴ አራተኛ አካል ወደ መኾን አላመጠቃትም። የዘርዐ ያዕቆብና ብጤዎቹ ድርሰቶች ከፈጣሪ በታች፥ ከፍጡራን በላይ ነች ቢሉም፥ እውነቱ ግን ከፍጡራን መካከል መኾኗ ነው።

«ቅዱስ አትናቴዎስ እንዲህ ብሎ ነበር፤ 'ወኢይቤ ሉቃስ ከመ ገብርኤልሂ መልአክ ተፈነወ ኀበ ድንግል ባሕቲታ አላ ይቤ ኀበ ድንግል እንተ ተፍኅረት ለብእሲ ዘስሙ ዮሴፍ። ከመ በብሂሉቱ ፍኀርተ ብእሲ ያግህድ ከመ እግዝእትነ ማርያም ብእሲት ይእቲ። - ሉቃስም ገብርኤል መልአክ ወደ ድንግል እንደ ተላከ ብቻ አልተናገረም፤ ስሙ ዮሴፍ ለሚባል ሰው ወደ ታጨች ድንግል ተላከ አለ እንጂ። ለሰው የታጨች ድንግል በማለቱም እመቤታችን ማርያም ለሰው ልትታጭ የተገባች ሴት (ድንግል) እንደ ኾነች አስረዳ።' (ሃይ. አበው 30፥22)።

«7.0 እመቤታችን ዐደራ የመሰጠቷ አመክንዮ

«ጌታችን ኢየሱስ 12 ዓመት እስኪሞላው ድረስ የቤተሰቡ ኀላፊ ዮሴፍ በሕይወት ነበረ፤ (ሉቃ. 2፥41-51)፤ መቼ እንደ ሞተ ባይገለጥም፥ በወንጌላት ውስጥ ከዚያ በኋላ ከቤተሰቡ ጋር ወይም ብቻውን የታየበት ስፍራ የለም። ጌታ 30 ዓመት ሞልቶት አገልግሎት ከጀመረ በኋላ ስም አጥፊዎች 'አበደ' ሲሉ ባወሩበትና ባስወሩበት ሐሜት መነሻ፥ ቅድስት እናቱ ልትፈልገው ወደሚያስተምርበት ስፍራ ስትመጣ ዮሴፍ አልተከተላትም። አብረዋት የመጡት፥ ወንጌል 'ወንድሞቹ' እያለ የሚጠራቸው የቤተሰቡ አባላት እነያዕቆብ ነበሩ፤ ዮሴፍ በሕይወት ኖሮ ቢኾን፥ እንደ ሌላው ጊዜ ኹሉ የእርሱ አብሯት መኾን አስፈላጊ በኾነበት በዚያ ወሳኝ ወቅት፥ ከጌታ እናት ጋር በተገኘ ነበር፤ ማር. 3፥20-35።

«እነዚህ ወንድሞቹ የተባሉት ግን፥ ከሙታን እስከ ተነሣበት ጊዜ ድረስ ሳያምኑበት የቆዩ ነበሩ፤ ዮሐ. 7፥5። በተሰቀለበት ዕለትም፥ ከገሊላ ጀምሮ ሲከተሉትና ሲያገለግሉት የነበሩ እነዚያ ሴቶች፥ ቅድስት ድንግል እናቱን ተከትለው የመከራዋና የሐዘኗ ተካፋዮች ሲኾኑ (ማቴ. 27፥55:56፤ ሉቃ. 23፥55) ወንድሞቹ የተባሉት ግን በአካባቢው አልታዩም። ከዚህ እውነታ በመነሣትም፥ መድኀኔ ዓለምን ወልዳ ለሰው ዘር ያበረከተችው እመቤታችን ከቤተሰብ አይዞሽ ባይና ደጋፊ፥ ጠባቂና ተንከባካቢ እንዳልነበራት መገንዘብ አያስቸግርም፤ ስለዚህም ነው ጌታ፥ ዮሐንስ ይንከባከባት ዘንድ ኀላፊነት የጣለበት። የጌታን እናት የመንከባከቡን ኀላፊነት በዐደራ የተቀበለው ዮሐንስም፥ 'ወእምይእቲ ሰዓት ነሥኣ ውእቱ ረድእ ወአእተዋ ቤቶ፤' (ዮሐ. 19፥27) እንደ ተባለ፥ ያኔውኑ ወደ ቤቱ ወሰዳትና የመንከባከቡን ዐደራ መወጣት ጀመረ።

«በዐውዱ የሚታየው ይኸው ነው፤ በዐውዱ ያለው ታሪክ ቅድስት ድንግል ማርያምንና ዮሐንስን የሚመለከት ብቻ ነው። ማርያም ለዮሐንስ ዐደራ ተሰጠች እንጂ፥ ዮሐንስ ለማርያም ዐደራ አልተሰጥቶም። ከዚህም እኛ ልንማር የምንችለው ነገር ሊኖር ይችላል፤ ልጅ አልባ የኾኑ ባልቴቶችን፥ ጧሪ፥ ደጋፊና ተንከባካቢ የሌላቸውን አዛውንት መርዳት እንዳለብን ያሳስበናል፤ ዘፀ. 22፥22-24፤ ኢሳ. 1፥17፤ ያዕ. 1፥27።

ለኦርቶዶክሳውያን መልካም ዜና!
ትምህርተ ክርስትና፥
በመላላክ በነጻ ይሰጣል እንደ ገና።

ለመማር ይፈልጋሉን?
ሙሉ ስምዎን፥
የመ.ሣ.ቍጥርዎን፥
ገልጸው ይጻፉልን።

አድራሻችን፡ - የመ.ሣ.ቍ. 56307
አዲስ አበባ ነው።

# ክርስቲያናዊ ምግባር

ከደምፀ ቃለ አብ

## ምዕራፍ 10
## «ኢትፍቱ»

### 1.0 መግቢያ

«የባልንጀራህን ቤት አትመኝ፤ የባልንጀራህን ሚስት፥ ሎሌውንም፥ ገረዱንም፥ በሬውንም፥ አህያውንም፥ ከባልንጀራህ ገንዘብ ኹሉ ማናቸውንም አትመኝ።» ዘፀ. 20፥17።

የሌላውን ገንዘብና ንብረት፥ ወይም ለራስ ያልተገባን ነገር ኹሉ፥ የራስ ገንዘብ እንዲኾን በሐሳብ አጥብቆ መሻት፥ ወይም መፈለግ ምኞት ይባላል። «ከሰማይ ካልተሰጠው ሰው አንዳች ሊቀበል አይችልም።» ዮሐ. 3፥27። ነገር ግን ገደብ የለሽ ፍላጎቱን ለማርካት፥ የሌላውንም ኾነ ለእርሱ ያልተገባውን ኹሉ ቢመኝ፥ ምኞትን ተከትለው ከሚፈጸሙ ድርጊቶች ጋር ተደምሮ ብቻ ሳይኾን ይህ ድርጊት በራሱ ኀጢአት ነው።

በጥቅሉ የባልንጀራን ወይም የሌላውን ሰው ቤት፥ ሚስት፥ ገንዘብና ንብረት ኹሉ «አትመኝ» የሚለው የመጨረሻውና ዐሥረኛው ትእዛዝ፥ እስካሁን ከተመለከትናቸው ከዘጠኙ ትእዛዛት ለየት ያለ ገጽታ አለው። ይኸውም ዘጠኙ ኹሉ ሊጠበቁም ኾነ ሊጣሱ የሚችሉት፥ በበነቢብና (በንግግርና) በገቢር (በድርጊት) ሲኾን፥ «አትመኝ» የሚለው ትእዛዝ ግን፥ መጠበቅም ኾነ መጣስ የሚችለው በኀልዮ (በሐሳብ) ነው።

ክርስቲያን ተብለን የምንጠራ ብዙዎች፥ የእግዚአብሔር ቃል በሚለው መሠረት ሳይኾን ባለማስተዋል ወይም በልማድ፥ በኀልዮ ለምንጥሳቸው የእግዚአብሔር ትእዛዛት ክብደት ስንሰጥ አይስተዋልም። በነቢብና በገቢር የምንጥሳቸውን ሕገጋተ እግዚአብሔር ግን፥ በአፈጻጸማቸው ከራሳችን ዐልፈው በሌሎች ፊት ስለሚገለጡና በኀጢአተኝነት ስለሚያስፈርጁን አክብደን እናያቸዋለን። በልባችን የተመኘነውን ክፉ ነገር በንግግር ካልገለጽነውና በድርጊት ካልፈጸምነው፥ ከእኛና ከእግዚአብሔር በቀር ማንም ሊያውቀው ስለማይችል ብዙም አያስጨንቀንም። ይኹን እንጂ በኀልዮ የሚሠራ ኀጢአት፥ በነቢብና በገቢር ከሚሠራው ኀጢአት ጋር እኩል ነው፤ በምንም አያንስም።

«ኢትፍቱ» የሚለው ትእዛዝ፥ በሰው ዐይን ታናሽ መስሎ ቢታይም፥ በእግዚአብሔር ፊት ግን ከሌሎች ትእዛዛት የሚያንስ አይደለም። ከዐሥርቱ ቃላት አንዱ ኾኖ መቈጠሩ፥ ከዘጠኙ ሕገጋት ጋር ያለውን እኩልነት ያሳያል። ጌታ ኢየሱስም በቅዱስ ወንጌል ይህንኑ አረጋግጧል፤ ማቴ. 5፥18፡19። ሐዋርያው ያዕቆብም በመልእክቱ፥ አንዱን ሕግ ጠብቆ ሌላውን መጣስ፥ በኹሉ ተጠያቂ እንደሚያደርግ በመግለጡ፥ የትእዛዛቱን ኹሉ እኩልነት አስረድቷል፤ ያዕ. 2፥10።

ይህን ትእዛዝ የእግዚአብሔር ቃል በሚያስተምረው መሠረት ማወቅ፥ ለትእዛዛቱ ያለንን የተዛባ አመለካከት ለማስተካከል ከማገዙም በላይ፥ በአስመሳይነት ሳይኾን፥ በፍጹም ሐሳባችን እግዚአብሔርን ማምለክ የሚገባን መኾኑንም ያስገነዝባል ብለን እናምናለን።

### 2.0 ሕጉ የሚለው: -

#### 2.1 የባልንጀራህን ሚስት አትመኝ

በጋብቻ የተጣመሩ ወንድና ሴት፥ በሕይወት ዘመናቸው ኹሉ በሕገ ጋብቻ የታሰሩ ናቸው። በሕይወት እስካሉ ድረስ፥ የተጠመዱበትን የጋብቻ ቀንበር አውልቀው በመጣል፥ የሌላ ሰው መኾን አይችሉም፤ ሮሜ 7፥2፡3።

የባልንጀራን ሚስት ወይም ባል የራስ የኑሮ ጓደኛ ለማድረግ ማሰብና መፈለግ፥ የእግዚአብሔር ፈቃድ የኾነውን ጋብቻዊ ጥምረት ለማፍረስ እንደ ማሴር ይቈጠራል። እግዚአብሔር፥ «መፋታትን እጠላለሁ» (ሚል. 2፥16) ሲል፥ ለጋብቻ መጽናት ያለውን የማያወላዳ አቋም፥ በቃሉ በኩል ስለ ገለጠ፥ የሌላውን ሰው ሚስት ወይም ባል መመኘት፥ ለሕገ እግዚአብሔር ተገዥ አለመኾን ነው።

ያገቡም ኾኑ ያላገቡ፥ የባልንጀራቸውን (የሌላን ሰው) ሚስት ወይም ባል ይመኙ ይኾናል። በተለይ ያገቡቱ እንዲህ ቢያደርጉ፥ ካላገቡቱ ይልቅ የባሰ ጥፋት የፈጸሙ መስሎ ቢታይም፥ ድርጊቱ በየትኛውም ወገን ይፈጸም፥ በእግዚአብሔር ፊት ኀጢአት፥ በሰውም ዘንድ ነውረኛ ተግባር ነው።

በመጽሐፍ ቅዱስ እንደ ተመዘገበው፥ ንጉሥ ዳዊት ስምንት ያህል ሚስቶች ነበሩት፤ 1ሳሙ. 18፥27፤ 25፥42፡43፤ 2ሳሙ. 3፥2-5፤ 11፥27። በመጨረሻ ላይ የምትጠቀሰው ቤርሳቤሕ፥ «... የባልንጀራህን ሚስት ... አትመኝ» (ዘፀ. 20፥17) የሚለውን ትእዛዝ አፍርሶ፥ ኀጢአቱን ለመሸፈንና ምኞቱን ለመፈጸም ሲል፥ ባሏን አስገድሎ የጠቀለላት ሚስቱ ናት። «ነገር ግን ዳዊት ያደረገው ነገር ኹሉ በእግዚአብሔር ፊት ክፉ ኾነ።» 2ሳሙ. 11፥27።

ዳዊት የነበሩት ሚስቶች ሳያንሱት፥ ኦርዮንን አስገድሎ፥ ሚስቱን ቤርሳቤሕን በተጨማሪ ሚስትነት መጠቅለሉ፥ የእግዚአብሔርን ነገር እንደ ማቃለል ተቈጥሮበታል፤ 2ሳሙ. 12፥9። ስለ ኀጢአቱም፥ ከቤቱ ክፉ ነገር በማስነሣትና ሚስቶቹን ዐይኑ እያየ በቅርብ ዘመዱ በማስነወር እንደሚቀጣው፥ እግዚአብሔር በነቢዩ በናታን በኩል ነግሮታል፤ (ቍ. 10-12)። ይኹን እንጂ ዳዊት ምልስ በመኾኑ ጥፋቱን አምኖ፥ «እግዚአብሔርን በድያለሁ» (ቍ. 13) በማለት ንስሓ በመግባቱ፥

እግዚአብሔር ኀጢአቱን ይቅር ብሏል። ዳዊት የሠራቸው ክፉ ነገሮች (ዝሙትና ነፍስ ገዳይነት) በኦሪት ሕግ መሠረት የሞት ቅጣት የሚያስበይኑበት ቢኾኑም (ዘሌ. 20፥10፤ 24፥17)፥ «አትሞትም» ተብሏል፤ (ቊ. 13)።

ዳዊት ኀጢአቱ ይቅር ቢባልና፥ ከሞት ፍርድ ቢድንም፥ የክፉ ሥራውን ብድራት ግን በሕይወተ ሥጋ እያለ አይቀበልም ማለት አይደለም፤ ገላ. 6፥7:8። ገና በመጀመሪያ ነቢዩ ናታን ወደ ዳዊት መጥቶ ጥፋቱን በምሳሌ ማስረዳት ሲጀምር፥ በምሳሌው የተጠቀሰው ባለጠጋው ሰው፥ ብዙ በጎችና ላሞች እያሉት፥ የድኻውን አንዲት ታናሽ በግ ወስዶ በእርሷ እንግዳውን ማስተናገዱ፥ ዳዊትን እጅግ አስቈጥቶት ነበር። በመኾኑም፥ «ናታን፥ ሕያው እግዚአብሔርን! ይህን ያደረገ ሰው፥ የሞት ልጅ ነው። ይህን አድርጓልና፥ አላዘነምና ስለ አንዲቱ በግ አራት ይመልስ አለው።» (ቊ. 5)። ዳዊት፥ ያ ሰው ራሱ መኾኑን ሳያውቅ እንደ ፈረደው ኹሉ፥ የዘራውን አራት እጥፍ በአራቱ ልጆቹ ላይ በደረሰው ክፉ ነገር ያጨደው ይመስላል። ሦስቱ ልጆቹ አምኖን፥ አቤሴሎምና አዶንያስ ክፉ አሟሟት ሞቱ፤ 2ሳሙ. 13፥28:29፤ 18፥14:15፤ 1ነገ. 2፥24:25። ዳዊት ከአንደኛዋ ሚስቱ ከመዓካ የወለዳት፥ የአቤሴሎም እኅት ትዕማር፥ ከሌላው ሚስቱ ከአኪናሆም በወለደው ልጅ በወንድሟ በአምኖን ተደፈረች፤ 2ሳሙ. 13፥1-19። ከዚህ ባሻገር እግዚአብሔር እንደ ተናገረው፥ «በእስራኤል ኹሉ ፊትና በፀሓይ ፊት» (2ሳሙ. 12፥12) ልጁ አቤሴሎም ከዳዊት ሚስቶች ጋር ተኛ፤ 2ሳሙ. 16፥21:22። ያገቡም ኾኑ ያላገቡ ሰዎች፥ ይህን ስሕተት ፈጽመው እንዳይገኙና ወደ ባሰ ፍርድ እንዳይገቡ ከዳዊት ሕይወት ብዙ ሊማሩ ይገባል።

### 2.1.1 ጤናማ ያልኾነ ማየት ወደ መመኘት ያደርሳል

ሰው አንድን ነገር በጣም እንዲወድና እንዲመኝ ከሚያደርጉት የስሜት ሕዋሳቶቹ መካከል ዐይን ዋናው ነው። ይህ፥ «ከማየት አይጠግብም» (መክ. 1፥8) የተባለለት የአካላችን ክፍል፥ ሊያይ የሚገባውን መልካምና የሚያንጽ ነገር ብቻ እንዲያይ መደረግ አለበት።

ሳይመርጥ ኹሉን እንዲያይ ከተፈቀደለትና መረን ከተለቀቀ ግን፥ መንፈሳዊ ሕይወታችንን ትልቅ አደጋ ላይ መጣሉ አይቀርም። ዐይን የውጫዊውን ዓለም ተጽዕኖ ወደ ልባችን ለማስገባትና ያንኑ ተከትለን እንድንሄድ ለማድረግ ኀይል እንዳለው መታወቅ አለበት። ልባችንን አጥብቀን መጠበቅ የሚገባንን ያህል (ምሳ. 4፥23)፥ ዐይናችንንም አጥብቀን መጠበቅና መቈጣጠር የሚገባንም ለዚህ ነው።

ብዙ ጊዜ ሰው፥ ተቃራኒ ጾታውን ለጾታዊ ፈቃዱ የሚመኘው ከማየት ተነሥቶ ነው። በልቡ የተለየ ሐሳብ የያዘ ካልኾነ በቀር ማንኛውም ሰው ተቃራኒ ጾታውን ገና ሲመለከት እይታው ጤናማ ሊኾን ይችላል። ኾኖም በተመለከተው ሰው አንድ ነገር ሲማረክ ዐይነ ውሃው ይለወጣልና እይታው ወደ ምኞት ያድጋል። ፈቃደ ሥጋውን የመፈጸም ፍላጎቱም እየናረ ይመጣል። እዚህ ወጥመድ ውስጥ የገባ ሰው፥ የኹኔታዎች አለመመቻቸት ቢያግዱት እንጂ፥ ምኞቱን ከመፈጸም ወደ ኋላ አይልም።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፥ «ወደ ሴት ያየ ኹሉ፥ የተመኛትም፥ ያን ጊዜ በልቡ ከእርስዋ ጋር አመንዝሯል።» (ማቴ. 5፥28) ሲል እንደ ተናገረው፥ በመመኘት የሚደመደም እይታ አመንዝራነት ነው። ዳዊት ከቤርሳቤሕ ጋር በዝሙት ለመውደቅ የበቃው፥ በሰገነቱ ላይ ሲመላለስ፥ እርስዋ ገላዋን ስትታጠብ ስላያትና መልክ መልካምነቷ እይታውን ወደ ምኞት ስለለወጠበት ነው፤ 2ሳሙ. 11፥2። እዚህ ላይ ያላገቡ፥ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ እየኖሩ ለማግባት ዝግጁ በኾኑበት ሰዓት፥ አይተው ያሰቡትንና የወደዱትን ሰው የኑሮ ጓደኛቸው እንዲኾን መፈለጋቸው፥ ዐላፊ አግዳሚውን ኹሉ እያዩ ከመመኘት ጋር መምታታት የለበትም፤ (ጦራ ቊጥር 29 ገጽ 21:22 ተመልከት)።

ከተቃራኒ ጾታ ውጪ ባሉ ጕዳዮችም ቢኾን፥ የሰው ድርጊት ወደ ገቢራዊ ኀጢአት የሚሸጋገረው፥ ከማየት ተነሥቶ እንደ ኾነ ይታወቃል። የእስራኤል ልጆች የኢያሪኮን ቅጥር በታላቅ ጩኸት ከናዱት በኋላ፥ እርም የኾነውን (እንዲደመሰስ እንጂ ለራሳቸው እንዳይወስዱ የተከለከለውን) ነገር ከመውሰድ እንዲታቀቡ እግዚአብሔር ትእዛዝና ማስጠንቀቂያ ሰጥቶ ነበር፤ ኢያ. 6፥15-21። ይኹን እንጂ አካን የተባለው ሰው፥ አምላካዊውን ትእዛዝና ማስጠንቀቂያ ቸል ብሎ፥ ከእርሙ በመውሰድ በደለ። የእስራኤልን ልጆች አስጨንቆ የያዛቸውና በጠላቶቻቸው ፊት በድል አድራጊነት እንዳይቆሙ ያደረጋቸው ኀጢአቱ ሲገለጥ፥ ለኢያሱ፥ «በዘረፋው መካከል አንድ ያማረ የሰናዖር ካባ፥ ኹለት መቶ ሰቅል ብር፥ ሚዛኑ ኀምሳ ሰቅል የኾነ ወርቅ <u>አይቼ ተመኘኋቸው ወሰድኋቸውም፤»</u> (ኢያ. 7፥21) ሲል እንደ ተናዘዘው፥ እግዚአብሔር የከለከለውን ነገር አይቶ ተመኘ፤ የተመኘውንም ወሰደ።

### 2.1.2 የሰውን ጤናማ እይታ ከሚለውጡ ድርጊቶች መቈጠብ ይገባል

የአንድ ሰው ጤናማ እይታ ወዳልተፈለገ አቅጣጫ የሚቀየረው፥ 'በተመልካቹ ሰው ደካማነት ብቻ ነው' ብሎ ለመደምደም ያስቸግራል። የሚያዩት ሰውም ባለው ተፍጥሮኣዊ ውበት ላይ የሌላውን ትኵረት ለመሳብ የሚጠቀማቸው ልዩ ልዩ መስሕቦች፥ እይታን በመለወጡ በኩል ከፍ ያለ ሚና ይጫወታሉ። ይህ በተለይ በሴቶች ዘንድ ጐልቶ ይታያል። የወንዶችን ትኵረት ለመሳብና በምኞት ዐይን እንዲመለከቷቸው ሲሉ

የሚያደርጉት ቅጥ ያጣ መጊያጊያጥ፥ አለባበስና አረማመድ ለብዙ ወንዶች ወጥመድ ነው፤ ምሳ. 7፥10።

ክርስቲያን ሴቶች በዚህ በኩል ለወንዶች መሰናክል ወይም ወጥመድ ኾነው እንዳይገኙ፥ የእግዚአብሔር ቃል በሚያዝዛቸው መሠረት ሊመላለሱ ይገባል፤ 1ጢሞ. 2፥9:10፤ 1ጴጥ. 3፥3። በማንኛውም መንገድ ለሌላው ሰው መሰናክል ምክንያት ኾኖ መገኘት፥ በእግዚአብሔር ፊት የሚያስጠይቅ ከባድ ጥፋት ነው፤ ማቴ. 18፥5-7። ሴቶች፥ 'እኛ ብንለብስና ብናጌጥ ለራሳችን ነው፤ ወንዶች እኛን ምን አሳያቸው?!' የሚል ሰንካላ ምክንያት በማቅረብ፥ በማሰናከያነት ከመጠየቅ ሊድኑ አይችሉም። ወንዶቹም ቢኾኑ፥ በምኞት ወጥመድ ለመያዛቸው፥ የሴቶቹን መስሕባዊ አለባበስና አረማመድ ምክንያት አድርገው በማቅረብ ከተጠያቂነት ነጻ አይኾኑም። አዳም፥ «ከእኔ ጋር እንድትኾን የሰጠኸኝ ሴት እርስዋ ከዛፉ ሰጠችኝና በላሁ።» በማለት በሔዋን ላይ፥ ሔዋንም፥ «እባብ አሳተኝና በላሁ» በማለት በእባብ ላይ ጥፋታቸውን መላከካቸው፥ ምክንያተ ስሕተት በኾኗቸው ላይ ብቻ አስፈርዶ እነርሱን ነጻ አላደረጋቸውም። አሰናካዩም ተሰናካዩም ተፈርዶባቸዋል፤ ዘፍ. 3፥12-19።

## 2.2 የባልንጀራህን ገንዘብና ሀብቱን ኹሉ አትመኝ

በዚሁ በዐሥረኛው የሕግ አንቀጽ ውስጥ፥ የባልንጀራችንን ሚስት ብቻ ሳይኾን ማናቸውንም ሀብቱንና ገንዘቡን እንዳንመኝ ታዘናል። 'ምኞት አይከለከልም' የሚለውን የሰነፎች ብሂል እንደ እውነት ቈጥሮ፥ ሰው ጥሮ ግሮ ያገኘውን፥ ከወላጆቹ በውርስ የተላለፈለትንና በመሳሰለው መንገድ ያፈራውን፥ ቤቱን፥ ተንቀሳቃሽና ቋሚ ንብረቱን፥ ድርጅቱን፥ ሥራውን፥ ገንዘቡንና በአጠቃላይም ኑሮውን ኹሉ የራስ እንዲኾን መፈለግ፥ በእግዚአብሔር ፊት ኀጢአት ነው።

የሌላን ሰው ሀብት የሚመኙ፥ ያጡ የነጡ ድኾች ብቻ አይደሉም። በቂና ከበቂ በላይ የተደላደለ ኑሮ ያላቸው ኹሉ፥ ገደብ የለሽ ፍላጎታቸውን ለማርካት፥ ባላቸው ላይ ለመጨመርና ከእነርሱ በላይ ከሚኖረው ሰው ጋር ለመስተካከል አሊያም በልጦ ለመገኘት ሲሉ፥ የሌላው ሰው ሀብት የእነርሱ እንዲኾን ይመኛሉ። ነገር ግን ድኻም ይኹን ሀብታም በማንኛውም ምክንያት፥ ከሌላው ሰው ሀብት ወይም ንብረት መካከል ማናቸውንም እንዳይመኝ እግዚአብሔር አዝዟል።

አንዳንዶች፥ ኑሮአቸው የተሟላ ኾኖ ምንም ሳይጐድልባቸው፥ እታች ወርደው ከእነርሱ በኑሮ እጅግ የሚያንሰውን ሰው ንብረት መመኘታቸው የተለመደ ነው። የእስራኤል ንጉሥ አክዓብ በኑሮው ምንም የጐደለበት ሳይኖር፥ የተራውን ኢይዝራኤላዊው የናቡቴን የወይን ቦታ ተመኘ። 'ለዋጩን ቦታ አሊያም ግምቱን ገንዘብ ልስጥህና በቤቴ አቅራቢያ የሚገኘውን የወይን ቦታህን ስጠኝ' ሲል ሊያግባባው ቢሞክር ፈቃደኛ ኾኖ አልተገኘም። በዚህ ምክንያት እጅግ መናደዱን የተመለከተችው የንጉሡ ሚስት ኤልዛቤል፥ ናቡቴን አስገድላ፥ ለባሏ የተመኘውን የወይን ቦታ አወረሰችው፤ 1ነገ. 20፥1-16።

በጽኑ ምኞት የተያዙ ሰዎች ኀይል በእጃቸው ስላለ የተመኙትን ከመፈጸም የሚከለክላቸው የለም። የፈለጉትን ለማግኘት በሚያደርጉት ጥረት ብዙ በደልና ግፍ ይፈጽማሉ። «ስለ ድኾች መከራና ስለ ችግረኞች ጩኸት ... አሁን እነሣለሁ» ባለው በእግዚአብሔር እጅ መውደቃቸውና ፍዳቸውን መቀበላቸው ግን አይቀርም። ኤልዛቤል በእጇ ያለውን ኀይል አለአግባብ በመጠቀም፥ ናቡቴን አስወግራ፥ የወይኑን ቦታ ለባሏ በማውረስ ምኞቱን ልትፈጽም የቻለች ቢመስልም፥ ፍጻሜዋ ግን እግዚአብሔር በነቢዩ በኤልያስ አፍ እንደ ተናገረው፥ የከፋ ኾኗል፤ 1ነገ. 20፥23፤ 2ነገ. 9፥30-37።

ዛሬም ቢኾን፥ «በመኝታቸው ላይ በደልን ለሚያስቡ፥ ክፋትንም ለሚያደርጉ ወዮላቸው! ኀይል በእጃቸው ነውና ሲነጋ ይፈጽሙታል። በዕርሻው ላይ ይመኛሉ፥ በግዴታም ይይዙታል፤ በቤቶችም ላይ ይመኛሉ፥ ይወስዱአቸውማል፤ ሰውንና ቤቱን፥ ሰውንና ርስቱንም ይነጥቃሉ። ስለዚህ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል: - እነሆ! በዚህ ወገን ላይ በክፉ ዐስባለሁ።» ሚክ. 2፥1-3።

## 3.0 ምኞት የኀጢአት እናት፥ የሞት አያት ናት፤

እያንዳንዱ ሰው፥ «በራሱ ምኞት ሲሳብና ሲታለል»፥ ኀጢአትን ወደ መሥራት እንደሚያዘነብል የታወቀ ነው። ምኞት ፀንሳ ኀጢአትን፥ ኀጢአትም ካደገች በኋላ ሞትን ትወልዳለች፤ ያዕ. 1፥14:15። ይህ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትምህርት፥ የጥፋት መንገድ መነሻው ምኞት፥ ከዚያም በኀጢአት በኩል ዐልፎ መድረሻው ሞት መኾኑን ያስረዳል።

ሔዋን፥ እግዚአብሔር እንዳይበሉት ካዘዘው፥ «መልካምንና ክፉን ከሚያስታውቀው ዛፍ» ወስዳ የበላችውና ለባሏም የሰጠችው፥ በምኞት ተታልላ ነው። እግዚአብሔር ከእርሱ እንዳይበሉ የከለከለውን ዛፍ፥ እባብ፥ «ለመብላት ያማረ እንደ ኾነ፥ ለዐይንም እንደሚያስጐመጅ፥ ለጥበብም መልካም እንደ ኾነ» አስመስሎ በማቅረቡ፥ ሔዋን ዛፉን ለመብላት ጐመጀች። መጐምጀቷ የዛፉን ፍሬ ወደ መብላት ኀጢአት አደረሳት። በመጨረሻም የኀጢአት ውጤት የኾነው ሞት ተከተላት፤ ዘፍ. 3፥1-21።

ጠላት ሰይጣን ሰውን ኀጢአት አሠርቶ፥ ከእግዚአብሔር መንገድ ለማስወጣት በመጀመሪያ የሚያደርገው፥ ክፉ ሐሳብን በሰው ልብ ውስጥ መጨመር ነው። ያ ክፉ ሐሳብም

የኑሮውን ጒድለትም በሚያገኘው ትርፍ ጊዜ እየሠራ ከመሸፈን በቀር የማንንም ገንዘብ አልተመኘም፤ ወይም የማንም ሸክም አልኾነም፤ የሐዋ. 20፥33-35፤ 2ተሰ. 3፥8።

ሌሎች ደግሞ በምኞት ኀጢአት በመጠላለፋቸው የተጣለባቸውን መንፈሳዊ ዐደራ በታማኝነት ለመወጣት አልቻሉም። የነቢዩ ኤልሳዕ ሎሌ ግያዝ ያደረገውን እንመልከት። የሶርያ ንጒሥ ሰራዊት አለቃ የነበረውን ንዕማንን፥ እግዚአብሔር በአገልጋዩ በኤልሳዕ እጅ በፈወሰው ጊዜ፥ ንዕማን በረከት ሊሰጠው ወደደ። ኤልሳዕ ግን ስመ እግዚአብሔርን ጠርቶ አልቀበልም አለ። ኹለቱ በዚህ ኹኔታ ከተለያዩና ንዕማንም ጒዞ ከጀመረ በኋላ፥ ግያዝ፥ ኤልሳዕ የቀረበለትን ስጦታ ባለመቀበሉ ተቈጭቶና ተመኝቶ፥ «... ሕያው እግዚአብሔርን በስተ ኋላው እሮጣለሁ፥ ከእርሱም አንዳች እወስዳለሁ አለ።» 2ነገ. 5፥20። ሄዶም ደረሰበትና ኤልሳዕ የላከው በማስመሰል፥ አንድ መክሊት ብርና ኹለት መለወጫ ልብስ ጠየቀ። እርሱም በጠየቀው ላይ አንድ መክሊት ብር አክሎ በመስጠት አሰናበተው። ግያዝ ይህን በስውር ቢያደርገውም ነገሩ በኤልሳዕ ዘንድ በመገለጡ፥ «እንግዲህስ የንዕማን ለምጽ በአንተ ላይ፥ ለዘላለምም በዘርህ ላይ ይጣበቃል አለው። እንደ በረዶም ለምጻም ኾኖ ከእርሱ ዘንድ ወጣ።» (ቊ. 27)።

የአስቆሮቱ ይሁዳ፥ ጌታን አሳልፎ እስከ መስጠት የደረሰው የገንዘብ ፍቅር ክፉኛ ስላደረበት መኾኑ ይታወቃል። በቢታንያ ለጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በተዘጋጀለት እራት ላይ፥ የአልዓዛር እኅት ማርያም (ማርያም እንተ እፍረት)፥ «ዋጋው እጅግ የከበረ የጥሩ ናርዶስ ሽቱ ንጥር ወስዳ የኢየሱስን እግር ቀባች፤ ... ቤቱም ከናርዶስ ሽቱ ሞላ።»። ይሁዳም፥ «ይህ ሽቱ ለሦስት መቶ ዲናር ተሸጦ ለድኾች ያልተሰጠ ስለ ምን ነው?» ሲል ጠየቀ። ወንጌላዊ ዮሐንስ እንደ ዘገበልን፥ «ይህንም የተናገረ ሌባ ስለ ነበረ ነው እንጂ፥ ለድኾች ተገድዶላቸው አይደለም፤ ከረጢትም ይዞ በውስጡ ከሚገባው ይወስድ ስለ ነበረ ነው።» ዮሐ. 12፥1-6።

**8.0 ቤተ ክርስቲያን ምኞት ቀስቃሽ ትምህርቶችን መቈጣጠር አለባት።**

በማወቅም ይኹን ባለማወቅ፥ ወይም የተቸገሩና ተስፋ ቢስ ሰዎችን ለማጽናናት፥ ወይም ሰዎችን የእግዚአብሔር ተከታይ ለማድረግ በአንዳንድ ወገኖች የሚሰጡ አንዳንድ ስብከቶች፥ መመኘትን በተዘዋዋሪ መንገድ የሚያበረታቱ ኾነው ተገኝተዋል። ዐላማቸውን ይፋ አውጥተው፥ «የብልጽግና ወንጌል» በሚል ስም ከሚታወቁት የእምነት ክፍሎች ውጪ የሚሰጠውን ማለታችን ነው። አንዳንድ ስብከቶች፥ 'ጌታን ብትከተል ከምድራዊ ችግርና ድኽነት ነጻ ትወጣለህ' ወደሚል አቅጣጫ ያዘመሙ ናቸው። እንዲህ ያለው ሰበካ፥ ለሰው ስሜት ቅሩብ በመኾኑ ለጊዜው ብዙ ሰሚዎችን መማረክ ይችል ይኾናል። በሂደት ግን የተባለላቸው ባለመፈጸሙ፥ ብዙዎች ወደ ኋላ በማፈግፈግ እግዚአብሔርን እስከ መተው ይደርሳሉ።

በመሠረቱ እግዚአብሔር እርሱን ስንከተል ከድኽነት አላቅቆ፥ ወደ ተንደላቀቀ ምድራዊ ኑሮ እንደሚያሸጋግረን ተስፋ አልሰጠንም። እንደ ፈቃዱ እየኖርን በሙያችን ብንሰማራ ግን፥ የእጃችንን ሥራ እንደሚባርክ ተናግሯል፤ ዘዳ. 7፥12-15፤ 28፥1-14።

በርደተ መንፈስ ቅዱስ የተቋቋመችው የመጀመሪያዋ ቤተ ክርስቲያን አባላት፥ «አንድ ልብ፥ አንዲትም ነፍስ» ስለ ነበሯቸው፥ ያላቸውን ጥሪት ኹሉ አንድ ላይ በማድረግ፥ በመካከላቸው ችግረኛ እስኪታጣ ድረስ በፍቅርና በመረዳዳት ይኖሩ እንደ ነበር ይታወቃል፤ የሐዋ. 4፥32-37። ነገር ግን በቤተ ክርስቲያን ላይ በደረሰው ታላቅ ስደት ምክንያት (8፥1)፥ ክርስቲያኖች ወደ ይሁዳና ሰማርያ አገሮች ከተበተኑ በኋላ ባሉት ዘመናት፥ በቤተ ክርስቲያን ድኾችም ሀብታሞችም በአባልነት ታቅፈዋል።

በክርስቶስ ያመኑት አባሎቿ ኹሉ፥ «በሰማያዊ ስፍራ በመንፈሳዊ በረከት ኹሉ» (ኤፌ. 1፥3) መባረካቸው እውነት ነው። በልዩ ልዩ ምክንያት ምድራዊ የኑሮ ደረጃቸው ግን ሊለያይ ይችላል። ስለዚህ ሀብትና ገንዘብ ያላቸው ክርስቲያኖች፥ ድኾቹን ክርስቲያኖች በገንዘባቸው ያገለግሉ ነበር፤ ሮሜ 15፥24-27፤ 1ቆሮ. 16፥1-11፤ 2ቆሮ. 9፤ ፊልጵ. 4፥14-18። ይኹን እንጂ በደፈናው ድኽነት የመረገም፥ ባለጠግነት ደግሞ የመባረክ ምልክት ተደርጎ መታየት የለበትም። ጌታን መከተልም ከድኽነት የማምለጫ መንገድ፥ ወይም ምድራዊ ትርፍ የማግኛ ዘዴ ተደርጎ ሊወሰድ አይገባም፤ 1ጢሞ. 6፥5።

ሐዋርያው ጳውሎስ፥ እግዚአብሔር የከለከለውን ነገር ኹሉ «መመኘት»፥ ለቅዱሳን የማይገባ ሥራ በመኾኑ፥ «በእናንተ ዘንድ ከቶ አይሰማ» ሲል ጽፏል። ይህን የተላለፈ ማንም ቢኖር ግን፥ «በክርስቶስና በእግዚአብሔር መንግሥት ርስት የለውም።» ኤፌ. 5፥3:5።

**9.0 በጎ ምኞት**

ክፉ ምኞት ኀጢአት እንደ ኾነ ኹሉ፥ በጎ ምኞት ደግሞ በክርስቲያኖች ሕይወት እንዲያብብና እንዲጐመራ የሚበረታታ መልካም ሥራ ነው። መልካም ምኞት፥ እግዚአብሔር ለክብራችን የወሰነውን መንፈሳዊ ነገር ኹሉ፥ ለራስም ለሌሎችም አጥብቆ መሻት ነው፤ ፊልጵ. 3፥7-11፤ ሮሜ 9፥1-3፤ 10፥1።

ከጥንት ጀምሮ የእግዚአብሔር ሰዎች መንፈሳዊ ነገሮችን ለማግኘት ተመኝተዋል፤ መልካም ነገርን መመኘታቸው ታዲያ፥ የመንፈሳዊ ርካታ ምንጭ ኾነላቸው እንጂ፥ ኀጢአት ኾኖ አልተቈጠረባቸውም፤ መዝ. 21፥2፤ ማቴ. 13፥17፤ ዮሐ. 8፥56።

መላእክቱ ሳይቀሩ መንፈሳዊ ምኞት እንዳላቸው ተጽፏል፤ 1ጴጥ. 1፥12። «በጎ ስጦታ

ኹሉ፥ ፍጹምም በረከት ኹሉ ከላይ ናቸው፤ ... ከብርሃናት አባት ይወርዳሉ፤» (ያዕ. 1፥17) ተብሏልና፥ መንፈሳዊ ነገሮችን እንድንፈልግ የሚያነሣሣን ቅሉ ራሱ እግዚአብሔር ነው። መጽሐፈ ኪዳንም፥ ቅዱሳን መላእክት እንዲሹት እንዲያመሰግኑትም መፈለግንም ማድረግንም የሚሰጣቸው ራሱ እግዚአብሔር እንደ ኾነ ሲገልጽ፥ «ዘያፈትዎሙ ለመላእክት የሐውጽዎ» ብሏል። እኛም መንፈሳዊ ነገርን እንድንመኝ ታዝዘናል፤ ማቴ. 6፥33፤ 7፥7፤ ዕብ. 12፥14፤ 1ጴጥ.2፥1-3። እግዚአብሔርም ለሚፈሩት ኹሉ ምኞታቸውን እንደሚፈጽም የታመነ ነው፤ መዝ. 145፥19።

## ማጠቃለያ

ከጮራ መንፈሳዊ መጽሔት ቍጥር 17 ጀምሮ እስከዚህ እትም ድረስ፥ «ክርስቲያናዊ ምግባር በተሰኘው በዚህ ዐምድ፥ የክርስቲያናዊ ምግባር መሠረት የኾኑትን ዐሥርቱ ትእዛዛትን፥ ከእግዚአብሔር ቃልና ከክርስቲያኖች ኑሮ አንጻር ለመመርመር ተሞክሯል። በተከታታይ የተሰጡት ትምህርቶች ለምእመናን መንፈሳዊ ሕይወት መታነጽ በረከት እንደ ኾኑ ተስፋ እናደርጋለን። በቀጣይ ደግሞ ጌታ ቢፈቅድ «አንቀጸ ብፁዓን» እየተባለ የሚታወቀውን የጌታን የተራራ ስብከት እናቀርባለን።

## መሠረተ እምነት ከገጽ 12 የዞረ

### 25.3 የኅሊና ምስክርነት

ከላይ የተገለጹትን ሦስት ምስክሮች የሚሰማና የሚታመንባቸው ሰው፥ በነፍሱ ምስክር እንዳለው የእግዚአብሔር ቃል ያረጋግጣል፤ 1ዮሐ. 5፥9:10።

1. በእግዚአብሔር ቃል ከተደገፈው አማናዊ ዕረፍትና ሰላም ሰጪ ጋር ካልተገናኘ በቀር፥ የሰው ኅሊና በምንም በምናምኑም ቢደለል፥ ዕረፍትና ሰላም ከቶ አይኖሩትም። የሰሜንን አቅጣጫ ጠቋሚ የኾነው የመሣሪያ ልሣን፥ ተፈላጊውን አቅጣጫ እስኪያገኝ ድረስ ሲዋልል እንደሚገኝ፥ እንደዚሁ ሰው ከላይ የተገለጹት ሦስቱ የሚሰጡትን ምስክርነት ሲቀበል ብቻ፥ የተቀበለው ቃለ እግዚአብሔር የኅሊና ዕረፍትን፥ የልብ ሰላምን፥ የመንፈስ ቅዱስ ደስታን፥ የአእምሮ መረጋጋትንና መስከንን ይሞላዋል፤ ማቴ. 11፥28፤ የሐዋ. 8፥35-39፤ 16፥30-34።
2. ኀጢአተኛነትንና ዓለማዊ ምኞትን ያስክደዋል፤ ቲቶ 2፥11-13።
3. የክርስቶስን ዳግም ምጽአት እንዲናፍቅ ያደርገዋል፤ ቲቶ 2፥11-13።
4. በዚህ ዘመን ራሱን እየገዛ በጽድቅና እግዚአብሔርን በመምሰል እንዲኖር ያስተምረዋል፤ቲቶ 2፥11-14።

## ማስገንዘቢያ

ሰዎች የኀጢአት ስርየት ያስገኛሉ በተባሉ፥ ሰውና መናፍስት ሠራሽ በኾኑ የባዶ ተስፋ ትምህርቶች እየተመሩ፥ አንዱ አንዱን ሲጨብጡ፥ የጨበጡትን ለቀው ሌላ ሲፈልጉ፥ ካንዱ ደብርም ወደ ሌላው ለመዞር የሚንከራተቱት፥ ባደረጓቸው ነገሮች ኹሉ ኅሊናቸው ስለማይረካና ስለማያርፍ ነው። ከገንዘባቸው፥ ከጊዜአቸው፥ ከጕልበታቸው ሳይኾኑ፥ የሚፈልጉትንም ሳያገኙ፥ በእነዚህና በእእምሮ መክሠራቸው ሳያንስ፥ የሕይወታቸው ጀምበር መጥለቅ፥ ወደ ባሰው ዘላለማዊ ገሃነመ እሳት ያሻግራቸዋል። እርስዎስ?

## ጸሎት

ከአብና ከመንፈስ ቅዱስ ጋር፥ ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ ተብለህ የምትመሰገን እግዚአብሔር ወልድ ሆይ! ለኔ ለኀጢአተኛው ቤዛ (ተለዋጭ) ትኾንልኝ ዘንድ ሰው ኾንህ። በሌላ በምንም እድን ዘንድ ተስፋ ያልነበረኝን የእኔን ኀጢአት፥ ልትሸከምና ልታስወግድ የእግዚአብሔር በግ ኾነሃልና፥ ዕዳ ሞቴን በሞትህ ከፈልህልኝ! ከጲላጦስ አደባባይ እስከ ቀራንዮ የፈሰሰው ደምህ፥ እኔን የሚያጥብ፥ ከኀጢአቴም የሚያነጻ ኀይል እንዳለው አምናለሁ። አንተ የእኔ ምትክ ኾነህ በመስቀታዊ ችሎት እኔ በምጠየቅበት ዕዳዬ ኹሉ ተለውጠህልኛልና፥ ተለዋጭ የኾንህለትን መንፈሴን፥ ነፍሴንና ሥጋዬን ከዛሬ ጀምሮ ላንተ አስረክቤአለሁ። ፈጣሪዬም ቤዛዬም በመኾንህ፥ በእኔ ላይ ለማዘዝ ሙሉ ባለሥልጣንና ጌታ የመኾን ሕጋዊ መብት ያለህ አንተ ብቻ እንደ ኾንህ ተገንዝቤአለሁ። ኹለንተናዬን በኹለንተናህ ዋጅተህ የራስህ አድርገኸዋልና፥ እኔ ለማንም ለምንም የመስጠት ሥልጣን የለኝም።

ስለ እኔ የተቈራረሰውን ሥጋህንና ስለ እኔ የፈሰሰውን ደምህን ከሚያመለክተኝ መንፈሳዊ ማእድህ፥ መንፈሳዊ ምግብ ይኾንልኝ ዘንድ በቅድስት ቤተ ክርስቲያን እየተገኘሁ በመቀበል መንፈሳዊ ኀይሌን ዐድሳለሁ፥ አጠነክራለሁ። አንተንም፥ ፈቃድህንም ይበልጥ በማወቅ ለመሞላትና እስከ አንተ ፍጹም ሙላት ለማደግ ዕለት ዕለት ቃልህን አነባለሁ፥ አጠናለሁ፥ እንደ ተማርሁትም ለመኖር እተጋለሁ። በየዕለቱም በጸሎት ራሴን ላንተ መስጠቴን አረጋግጣለሁ።

እስከ ቤዛ ቀን ድረስ የታተመብኝን፥ የዕውር መሪዬን መንፈስ ቅዱስን ወደ ማሳዘን፥ ወደ ማስቈጣት፥ ወደ ማስመረርም ከመድረስና መካን የምድረ በዳ ሕይወት ከመኖር ጠብቀኝ። ሞገስ በሚኾንልኝና መወደድን፥ መሰማትን በሚያስገኝልኝ፥ ጕልበት ኹሉ በሚንበረከክለት፥ አንደበት ኹሉ ሊጠራው በሚገባው፥ በሰማይ፥ በምድር፥ ከምድርም በታች ያሉት ኹሉ በሚርዱለት፥ እንኳን በዚህ ዓለም በሚመጣውም ዓለም የሚታካከለው በሌለው፥ ስቡሕ ወውዱስ ክቡርና ምስጉን በኾነው ስምህ ተማጽኜሃለሁ። ወልደ እግዚአብሔር ጌታ ኢየሱስ ሆይ! ከአብና ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ከዘላለም እስከ ዘላለም ክብር ለሚገባህ ለአንተ ክብር ምስጋና ስግደት ይኹን! አሜን።

# ናይ ድሕንነት አስተምህሮ

**ፍረ እምነት**
**ናይ ምድሓን ትምህርቲ ተከታሊ**
**ሓደ አስካል-ኣምልኾ**

እቲ ብጐይታ ብኢየሱስ ክርስቶስ ሞትን ትንሳኤን ኣቢሉ ዝሓለፈ፥ በቲ ነቲ ቀዳማዊ ኣዳም መሲሉ ዝተወልደሉ ብሉይ ኣነነቱ ሞይቱ ድሕሪ ምቕባሩ (ምስተቐብረ)፥ በቲ ንዳግማዊ ኣዳም ዘምስሎ ሓድሽ ህይወት ዝተንስአ ምእመን፥ ገና ኣብዚ ምድሪ'ዚ እናነበረ ክኸውን ይኽእል'ዩ:: ካብቶም ምስ ጐይታ ኢየሱስ ክርስቶስ ዝተሰቕሉ ሽፋቱ እቲ ሓደ (ከም ናይ ወለዲ ትውፊታዊ ታሪኽ ፈያታይ ዘየማን) ምስ ኣመነ ኣበውሽጢ ሕደት ደቓይቕ ምሟቱ ይፍለጥ'ዩ:: ካብኡ ትፅቢት ዝኽበር ኣገልግሎት ኣይነበረን ማለት'ዩ:: ኣብዚ ምድሪ'ዚ ገና እናነበረ ዘሎ ምእመን ግና ዝድለዮ ኣገልግሎት ስለ ዘሎ፥ ነዚ ኣገልግሎት'ዚ ከም ናይ እግዚኣብሄር ፈቓድ ብፍቕሪ ክዋፅኦ ይግብኦ እዩ::

ብዛዕባ ሕድሕድ ምእመን ኵለንተና፥ ወዲ ኣምላኽ ኵለንተንኡ በጃ ብመሃበ ተበጂውዎ እዩ'ሞ፥ ካብዚ ኣነነቱ'ዚ ንርእሱ ወይ ድማ ንኻልእ አትሪፉ ዘቕርዮ ክፍሊ የብሉን፤ መንፈሱን፥ ነፍሱን፥ ስግኡን ብናይ ወዲ ኣምላኽ ስጋ፥ ነፍስን፥ መንፈስን ተገዚኡ ወይ ኸኣ ተለዊጡ ኵለንተንኡ ናይ እግዚኣብሄር ገንዘብ ኮይኑ እዩ:: መንፈስ ቅዱስ እንትሕተመሉ'ውን ኣብ ልዕሊ'ቲ ምእመን ናይ እግዚኣብሄር በዓል መሰልነት ተረጋጊፁ እዩ፤2ቆሮ. 1÷21:22::

ስለዚ ነፍሲወከፍ ምእመን ከም ናይ ባዕሉ ወይድማ ከም ናይ ካልእ ፍቓድን ምክርን እንተይኮነስ፥ ናይ በዓል ቤትነት መሰል ከምዘለዎ ናይ እግዚኣብሄር ፈቓድን፥ ምክርን ብኹለንተንኡ ክነበረሉን ክሰርሓሉን ይግብኦ እዩ፤ 1ቆሮ. 6÷19:20:: «ኢተአምሩኑ ከመ ማኅደሩ ለመንፈስ ቅዱስ አንትሙ፥ ዘኀዱር ላዕሌክሙ፥ ዘነሣእክሙ እምኀበ እግዚአብሔር፤ ወኢኮንክሙ ለርእስክሙ፤ በሤጥ ተሣየጠክሙ:: ሰብሕዎ ለእግዚአብሔር በሥጋክሙ:: - ሰብነትኩም ቤተ መቕደሽ ናይቲ ካብ ኣምላኽ ዝተቐበልክምዎ ኣብ ውሽጥኹም ዘሎ መንፈስ ቅዱስ ከም ዝኾነ ዶ ኣይትፈልጡን ኢኹም እምበኣር ናይ ገዛእ ርእስኹም ኣይኮንኩምን:: በዋጋ ኢኹም ዝተዓደግኩም፥ ስለዚ ንኣምላኽ ብሰብነትኩም ኣኽብርዎ» ይብል:: እዚ ሃዋርያ'ዚ በቲ ንምእመናን ሮሜ ዝፀሓፎ መልእኽቲ «ካባና ንርእሱ ኢሉ ዝነብር ወይ ንርእሱ ኢሉ ዝመውት፥ ሓደ እኳ የለን፤ ብህይወት እንተ ነበርና ንጐይታ ኢና እንነብር፤ እንተ ሞትናውን ንጐይታ ኢና እንመውት:: ስለዚ ብህይወት እንተ ነበርና ወይ እንተ ሞትና ናይ ጐይታ ኢና:: - ወአልቦ እምውስቴትነ ዘለርእሱ የሐዩ፤ ወዘለርእሱ ይመውት:: ወእመኒ ሐየውነ ለእግዚአብሔር ነሐዩ:: ወእመኒ ሞትነ ለእግዚአብሔር ንመውት:: እመኒ ሞትነ ወእመኒ ሐየውነ ለእግዚአብሔር ንሕነ::» ኢሉ እዩ ሮሜ 14÷7:8::

ብተወሳኺ'ውን እዚ ሃዋርያ'ዚ በቲ ንቆሮንቶስ ዝፅሓፎ ካልኣይ መልእኽቱ፥ «ውእቱ ሞተ በእንተ ኵሉ ከመ እለሂ የሐይዉ እኮ ለርእሶሙ ዘየሐይዉ ዘእንበለ ለዝኩ ዘበእንቲኣሆሙ ሞተሂ፥ ወሐይወሂ::

እቶም ብህይወት ዚነበሩ፥ ነቲ ምእንትኦም ዝሞተን ዝተንስኣን ' ምበር ንገዛእ ርእሶም ምእንቲ ኸይነብሩ ክርስቶስ ኣብ ክንዲ ኵላቶም ሞተ::» ብምባል (2ቆሮ. 5÷15) እግዚኣብሄር ነቲ ኣብ ልዕሌና ዘለዎ ናይ በዓል ቤትነት መሰል ሕጋዊነት ብምርዳእታ ብምጥንኻር የብራህርህ:: «ምንባር» እንትበሃል ድማ ነቲ እንነብረሉ ጐይታ ብምሉእ ሓይልን ፈቓድን «ምስራሕ» (ምዕያይ) ከምዝኾነ እንትገልፅ «ተዓዲግኩም ኢኹም እሞ ... ብስጋኹም ንኣምላኽ ኣኽብርዎ» ይብለና::

ሓደ ምእመን፥ ከም ፈያታይ ዘየማን፥ ናይ ኢየሱስ ክርስቶስ ኣድሓኒነትን ጐይትነትን ድሕሪ ምቕባሉ ሽዑንሽዑ እንተዘይሞተ (እንተዘይደቀሰ)፥ በቲ ናይ እግዚኣብሄር ገንዘብ ምእንቲ ክኸውን ፈቓደኛ ኮይኑ ዘረከቦ፥ እግዚኣብሄር'ውን ዝተረከቦ ኵለንተንኡ ክፍርዮ ዝግባእ ፍረ ካብኡ ትጽቢት ከምዝግበረሉ ተረጋጊፁ እዩ:: «ብዙሕ ፍረ እንተ ተፍርዩ ኣቦይ በዚ ይኽብር እዩ፤ ንስኻትኹም ከኣ ደቀ መዛሙርተይ ምዃንኩም በዚ ተፍልጡ::» እንትብል ጐይታ ስለ ዝተዛረበ (ዮሃ. 15÷8) ካብቶም መንጎ ደቀ መዛሙርነትና ክነርድኣሎምን ንእግዚኣብሄር ኣብ ብክርስቶስ ኢየሱስ ኣቢልና ክንኸበረሉ ዝግባእ ናይ ፍረ ዘለላታት እቲ ሓደ ዘለላ «ኣምልኾ» እዩ:: ትሕዝቶ ኣምልኾትና፥ ኣምልኾና ኣበይ፥ ኣምልኾና ከመይ፥ ዝብሉ ሕቶታ ኣብዚ ርእሲ'ዚ ንምክታት ጐይታ ብዝረድኣና መጠን ክንፍትን ኢና::

**1. መእተዊ**

እቶም እግዚኣብሄር ካብ ናይ ምድሪ ኣህዛብ ዝፈለዮም ናይ ባዕሉ ህዝብን መጓሴኡ ኣባጊዑን እዮም፤ መዝ. 23÷1-6፤ 95÷7፤ 100÷3:: ብፅንዕ ቅልፅሙ ኣድሒኒዎሙ፤ ብዋጋ'ውን ዓዲግዎም እዩ እሞ፥ ብናይ መማኽርቲ ጉባኤ ምምሕዳር ኣየመሓዳድሮምን:: ብዛዕባ ነፃነቶም ዝተዋግአ፥ ዋጋ ድማ ዝኸፈለሎም ንሱ በይኑ እዩ'ሞ፤ ንዕኡ ጥራሕ ክነብርሉ፥ ንዕኡ

## ንስሐ ያልተገባበት ዕዳ

«በትምህርቱ የዳኑና ከሕይወት በር የደረሱ ብዙዎች ናቸው:: ... በድብ ፀር (በዘርዐ ያዕቆብ) ዘመን ዘብር ከምትባል ሀገር ጀምሮ ደብረ ብርሃን፡ ዝማ፡ ጕዘም እስኪደርስ፡ ከእነዚህ ሀገሮች በስተግራ በኩልና በንጉሡ አደባባይም ሁሉ ሰማዕትነታቸውን በመልካም ሰማዕትነትና በመንፈሳዊ ገድል ከፈጸሙት ውስጥ፡ ቍጥራቸውን ያወቅነው የቅዱስ ብፁዓዊ እስጢፋኖስ ወንድና ሴት ልጆች ሰማዕታትና ጻድቃን ጠቅላላ ድምር ፲፻፬ (1004) ነው:: የማናውቀውን እሱ ንብረቱን ይሰብስብ:: ...»

«ከኢትዮጵያ ጋር እየተፋረድሁ ነው
በዚያው ወር በ፳፰ ቀን፡ ከቀኑ ዐሥራ አንድ ሰዓት ላይ የነገሩ ትርጕም በማይታወቅ በአንድ ነገር ላይ እንደሚፋረድ ከብዙዎች ጋር ይሟገት ጀመረ:: ወንድሞች፡ ‘አባ ሆይ! ምንድን ነው የምትለው? ከሰዎች ጋር ስትሟገት እናይሃለን፤’ አሉት:: አፉን ከፈተና፡ ‘ምንድን ነው የምትሉት (ዝም በሉ) በመፋረድ ላይ እኮ ነው ያለሁት’ አላቸው:: ‘ከማን ጋር ነው የምትሟገተው? እዚህ ካንተ በቀር ሌሎች አናይም’ አሉት:: ‘እኔ ከኢትዮጵያ ጋር እየተፋረድሁ ነው፤’ አላቸው::»

ጌታቸው ኀይሌ (1996) ደቂቀ እስጢፋኖስ «በሕግ አምላክ» ኮሌጅቪል (ሚኒሶታ)፤ ከገድለ አበው ወአኃው ገጽ 220፡221 እና የአባ አበከረዙን ገድል ገጽ 276 የተወሰደ::

ዋጋ ብር 3.00